# ዝርዝር ርዕሶች

Table of content


| የመልዕክቱ ቁጥር | ርዕሶች | ገፅ |
|---|---|---|
| 0 | መቅድም/Forward | 6 |
| 1 | አሁን የሆነው ምንድነው?<br>{What Just Happened?} | 8 |
| 2 | ኢየሱስ ከእርሱ እንድታውቁ የሚፈልገው ነገሮች<br>{What Jesus wants you to know from Him} | 10 |
| 3 | አሁን ምን ማድረግ ነው የሚያስፈልገኝ?<br>{What do I need to do now} | 12 |
| 4 | ልጆችና እንሰሳት ሁሉ ምንድነው የሚሆኑት ?<br>{What happened to all the Children and Animals?} | 16 |
| 5 | እከሌና እከሌ  እኔ እዚህ ለመቆየት ፈልጌ ነው የቆየሁት ይላሉ?<br>So-and-so just told me that he CHOSE to stay here? | 17 |
| 6 | በምድር ላይ ለቀሩት ተጨማሪ መመሪያ<br>{More about the Remnant} | 19 |
| 7 | ከንጥቀት በኋላ ስለሚሆነው የተሰጠ ማብራርያና ማስጠንቀቂያ<br>{Explanatio and Instruction after the Rapture} | 21 |
| 8 | በእግዚአብሔር አቅርቦትና ጥበቃ ውስጥ እንዴት መቆየት እንደሚቻልና የከዳተኞች መኖር<br>{How to stay under GOD, provision and relying on GOD, Warning of Traitors} | 25 |
| 9 | ለማ ጥበቃ እንደማደርግና ለማን እንደማላደርግ<br>{Who I Can Protect and Who I Cannot Protect } | 30 |
| 10 | ኢጋንንቶች፣ የ ወደቁ መላዕክቶች፣ እሳተ ጎሞራና የገሃነም መለጠጥ<br>{Demons, Aliens, Volcanoes and Hell Expanded} | 33 |
| 11 | ንጥቀቱ ለፀሎትና ሰዎችን ለመጎብኘት እድል ይፈጥራል<br>The Raptur Allows to  Pray and Breifely Visit those Left Behind | 37 |
| 12 | ቦንቡ በወደቀ ቀን  …<br>{The Day the Bombs Fall} | 40 |
| 13 | ራዕይ ለምንድነው መፈፀም ያለበት?<br>{Why Revelation Must Be Fulfilled} | 44 |
| 14 | የሚመጣውን የመከራ ዘመን ማለፍ<br>{Surviving the Coming Tribulation} | 49 |
| 15 | በክርስቶስ ያለውን ህይወት ፈልጉ<br>{Seek LIFE In Jesus} | 53 |
| 16 | ሁሉን ነገር የምትተዉበት ጊዜ ነው<br>{It's Time to Let Go} | 54 |
| 17 | ኢየሱስን ተከተሉ - የአውሬውን ምልክት አትቀበሉ<br>{Follow Jesus – Do NOT Take the Mark of the Beast!} | 56 |
| 18 | የቀረው እጅግ ጥቂት ጊዜ ነውና ወደእኔ ኑ<br>{There is Very Little Time.Come to Me} | 58 |
| 19 | ለእናንተ ያለኝ ፍቅር እጅግ ትልቅ ነው<br>{How Great is My Love for You} | 60 |

20 ገንዘብና በራስ መተማመን ወይስ እኔን ? አሁን ምረጡ 64
{Money, Self-Reliance. or ME. You Must Decide}

21 በሥጋ ላይ አትታመኑ 66
{Put No Confidence In The Flesh}

22 የገሃነም መንጋዎች ወደ ምድር ከልል ተለቀዋል 69
{The Hordes of Hell Have Been Released}

23 ሰርን እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከኔ ሌላ የለም 71
{CERN I Am God Non Other}

24 ከአለም ጋር ያላቸውን ፍቅር አሁን መተው አለባቸው 72
{They must forget now their love affairs with the world}

25 በመከራው ዘመን ወደኋላ ለቀሩት አቅርቦትና መመሪያ 74
{Provision and Instruction For Those Left Behind}

26 የእግዚአብሔርን ይቅርታ ተቀበሉ 77
ACCEPT THE FORGIVENESS OF GOD

27 የመከራው ዘመን ካለፈ በኋላ ምን እንጠብቅ 80
What you have to look forward to once the Tribulation is over

- ✓ ልባችሁ የዙፋኑ መቀመጫ ነው
  Your heart is His Throne room
- ✓ ኢየሱስ መንግስተ ሰማይ መግቢያ በር ነው
  Jesus is the entery to Heaven
- ✓ ኢየሱስን በመንግስተ ሰማያት መገናኘት
  Joining Jesus in Heaven

28 በመንግስተ ሰማይ የሰዎች አገልግሎት፣ ፀሎትና ምስጋና 85
Heaven : People serving, praying and prasing

29 በመንግስተ ሰማይ ጨዋታ አለ 86
There is fun in Heaven

30 የኔ ተፈጥሮ ማበረታታት ነው- ስለዚህም ምህረትን አድርጌያለሁ 88
My nature is Courage – I give to you My mercy

- ✓ ኢየሱስ ስለ መንግስተ ሰማይ ሚስጥራትን ሊገልጥ ቃል ገብቷል
  Jesus Promises to Reveal the Secrets of Heaven
- ✓ በመንግስተ ሰማይ ህይወት ምን እንደሚመስል፣ ስለ ሚሊኒየም ፍንጭ
  What Life in Heaven is Like – Clues About the Millennium
- ✓ በሚሊኒየም ሞት አለ?
  Will there be death in the Millennium?"
- ✓ ጌታ ሆይ አምልኮስ?
  And what about worship, Lord?

31 በመንግስተ ሰማይ ነገሮች እንዴት ነው የሚከናወኑት? እዛ ምን አለ? 93
How do things work in Heaven? What is there

32 በመንግስተ ሰማይ - የመረዳት ስፋት፣ ደስታና ተግባቦት 98
Heaven: Dimensions of Awareness, Pleasure, Leasure and Communication

33 መለየት ያለመቻልና የመንግስተ ሰማያት ጨረፍታዎች 99
Troubling Discernment & Glimpses of Heaven

| | | |
|---|---|---|
| 34 | በመንግሰተ ሰማይ የሚሆነው እንዲህ ነው፡ ከኢየሱስ ጋር የሚኖራችሁ ግንኙነት<br>This is How it will be in Heaven: your relationship with JESUS | 102 |
| 35 | ለነፍሳችሁ ዕረፍት አግኙ<br>Rest for your Soul | 103 |
| 36 | ኢየሱስ የመታዘዝን ዋጋ ምን እንደሆነ ይናገራል<br>Jesus speaks the high value of Obedience | 105 |
| 37 | ኢየሱስ በመንግስተ ሰማይ ያለውን አምልኮ፣ምግብና መዝናኛ እንዴት እንደሆነ ይናገራል<br>Heaven : Jesus shares about worship, food and recreation | 107 |
| 38 | ፍቅር በመንግስተ ሰማይ የዋጋ መተመኛ ቅንጣት ነው<br>In Heaven, love is the valued particle | 111 |
| 39 | መንግስተ ሰማይ የማያቋርጥ ደስታ ያለበት ሥፍራ ነው<br>Heaven is a place of perpetual joy | 114 |
| 40 | የሚሊኒየሙ መንግስት<br>Governement in the Millennium | 116 |
| 41 | ህይወት ኢየሱስ በሚገዛበት በሚሊኒየሙ መንግስት<br>Life during Jesus' rule during the Millennium | 118 |
| 42 | በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደምንጠመቅ<br>How to be Baptized in the Holy Spirit | 122 |
| 43 | ስለ ሥጋ ወደሙ አወሳሰድ የተሰጠ መመሪያ<br>Instruction about Communion | 124 |
| 44 | ከአጋንንት እሥራት ነፃ ለመውጣት የሚደረግ ዝግጅት<br>How to prepare for deliverance of demonics spirits | 127 |

# መልዕክት አንድ
# አሁን የሆነው ምንድነው?

{What has just happened?}

ይህችን ትንሽ መፅሐፍ የምታነቡት ኢየሱስ ራሱ በሰማይ ላይ ከታየ በኋላ ከሆነ፣ አሁን እውነቱን ስላወቃችሁ ውሳኔ ለመስጠት ጊዜው ነው፡፡ ኢየሱስ ይህ እንደሚሆን በነቢያቶቹ በኩል ለብዙ ዘመናት ለአለም ሁሉ ሲያስጠነቅቅ ቆይቷል፡፡ እርሱም ጊዜው እንደተቃረበ ለማሳየት በየጊዜው እየጨመሩ በሚሄዱ ብዙ ምልክቶችና ክስተቶች፣ ይኸውም በሰማያት፣ በምድር፣ በአየር ንብረት ሁኔታ፣ ብዛት ባላቸው የእንሰሳት ሞት፣ በሱናሜዎችና በመሬት መንቀጥቀት በኩል ለብዙ አመታት ሲያስጠነቅቀን ነበር፡፡

ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡፡ "እኔ ይህንን ሁሉ ነግሬያችሁ ነበር፡፡ በሰማይ ደመና ስመጣ ሰው ሁሉ እንደሚያየኝ፡፡ ሰው ሁሉ ሲባል ሰው ሁሉ ማለት ነው፡፡ በፍፁም ድብቅ አይሆንም፡፡ ይህንን ያደረግሁት ያልተቀበሉኝ ህዝቦቼ እንዲያዩኝና እንዲያለቅሱ በማሰብ ነው፡፡ ነገዶች ሁሉ ያዝናሉ አይልም?

*<u>በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፡፡</u> (ማቴዎስ 24፡30)*

*<u>መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን። እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን። ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ። አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል</u>።(ራዕይ 1፡6-8)*

እናም አሁን በመጨረሻው መጣ፡፡ ይህ ክስተት በተለምዶ ንጥቀት ይባላል፡፡ የንጥቀትም ዓላማ በእውነት እርሱን የሚወዱትንና ለእርሱም የኖሩትን ከምድር ላይ በመውሰድ፣ ከሚመጣው መከራ ለመታደግና በሰማይ እንዲኖሩ ለማድረግ ነው፡፡

ስለዚህም አሁን በምድር ላይ ተስፋፍቶ በሚገኘው ኃጢያት ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ጀምሯል፡፡ ይህንንም ቁጣ በራዕይ መፅሐፍ ላይ ተፅፎ ታገኙታላችሁ፡፡ በሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት በምድር ላይ ስለሚፈፀሙ ስለ ማህተሞች፣ ስለ ፍርድ መለከቶችና የእግዚአብሔር ቁጣ ፅዋዎች ሁሉ ተፅፎ ታገኛላችሁ፡፡

በዚህ ጊዜ ዋናው ትኩረት የሚደረገው በአይሁዶች ላይ ነው፡፡ ይህ ህዝብ ገና ከጅምሩ ልዩ ህዝብ አድርጎ እግዚአብሔር የመረጠውና ህዝቡም በመሰጠት እግዚአብሔርን ብቻ እንዲወድና እንዲያመልክ፣ ሌሎች ህዝቦች ማምለክ የጀመሩትን አማልክቶች እነዚህም ኢጋንንቶችን እንዳያመልክ የተከለከለ ልዩ ህዝብ ነው፡፡

"ይህንን ያደረኩት ህዝቤ ማን እንደሆንኩ እንዲውቁ ነው፡፡ እኔን በግልፅ ካላዩና ማን መሆኔን ካላወቁ ንስሐ ሊገቡ አይችሉም፡፡ ከሰማይ ስመጣ ባዩኝ ጊዜ ሳይቀበሉኝ በመቅረታቸው በሰሩት ኃጢያት እስከ መቅኒ አጥንታቸው ድረስ በፀፀት ይመታሉ፡፡"

"በንጥቀት ጊዜ በሰማይ ላይ ሆኜ እታያለሁ እንጂ እግሮቼ ምድርን አይረግጡም፡፡ ህዝቤ እኔን ስላልተቀበሉኝ ያዝናሉ፣ ያለቅሳሉ፡፡ አህዛብ ከእኔ ጋር ወደ መንግስተ ሰማይ ሲወሰዱ ህዝቤ ግን በዚሁ ምድር ላይ ይተዋሉ፡፡ ከዚያም በኋላ የገሃነም ደጆች በሙሉ ተፈተው ወደ ምድር ይገባሉ፡፡ ይህም የመከራው ዘመን ጅማሬ ነው፡፡ አረጋግጥላችኋለሁ ሰይጣን ክፉ እቅዱን በምድር ላይ ተግባርያዊ ለማድረግና የክርስቶስ ተቃዋሚውን በሥልጣን ላይ ለማውጣት ጊዜ አይፈጅበትም፡፡"

"ምድር እንደ ሰከረች ትሆናለች፡፡ አክስለቴተሩ የሚያናጋው (CERN -ሰርን የሚለውን መልዕክት ይመልከቱ) የመሬትን ዛቢያ ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ፕላኔቶችን ጭምር ነው፡፡ እንዲሁም የኒብሩና የአስተሮይዶች ወደ ምድር መቅረብ ሌላው ተጨማሪ ምክንያት ነው፡፡ ሁሉም ገሃነም ይፈታል አላልኩም? ስለዚህ ነው ሁሉም ክስተቶች በአንድ ላይ በመከናወን የምድርን ፍርድ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲፈፀም ለማድረግ ታስቦ የተደረገው፡፡"

"አይሁዶች የምወዳቸውን ያህል ከስስትና ሰውን ለጥቅማቸው ጉዳይ ከማሳመን ከሚያደርጉት ጥረት በቀር በምንም መልኩ ንፁህ ሆነው አልተገኙም፡፡ ስለዚህም ፍርዱ የሚፈፀመው በሁለት እጥፍ ዓላማ ነው፡፡ የመጀመሪያው እኔን ስላልተቀበሉኝ ሲሆን ሌላው ደግሞ በንግድ ስምምነት ወቅት ከእኔ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ቸል ስላሉ በዚህ ምድር ስለሚፈሰው የፍጥረታት ደም ሁሉ ተጠያቂ ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠያቂ መሆን አለባቸው፡፡ ፍፁም ተጠያቂ ናቸው፡፡ በዚህ ምድር ላይ በዚህ ወቅት የተገኙት ሌላው ምክንያት ለፍርድ ሲሆን እነሱ ባዘጋጁት አልጋ ላይ መተኛት አለባቸው፡፡"

የመጨረሻ ሥራውን የሚያጠናቅቀው የህዝቡን የአይሁድን ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን ፈተናው የሚመጣው በምድር ለቀረው ሰው ሁሉ ነው፡፡ ፈተናውም በመጨረሻው ሰዓት ኃጢያታቸውን ተናዘው ወደእርሱ ይመለሱ እንደሆነ ነው፡፡ ከፍጥረት ጀምሮ እንደነበረው ሁሉ በዚህ ወቅትም ሁሉም በእግዚአብሔር ዕይታና ልብ ውስጥ ይሆናሉ፡፡ ማንም እርሱን የሚጠይቅ ቢኖር ተቀባይነትን ያገኛል፣ ነፍሱ ትድናለች፣ በሞትም ወደ መንግስተ ሰማይ ይሻገራል፡፡

ነገር ግን ወደ እርሱ በሙሉ ልባችሁ መምጣት አለባችሁ፡፡ ይህም በሁሉ ነገር በእርሱ ላይ ብቻ እንድትደገፉና ከእርሱ ዘንድ ብቻ ከብካቤ እንድታገኙ ነው፡፡ በዚህም የሚያስፈልጋችሁን እንዲያቀርብላችሁ፣ ሲያስፈልግ ከጠላት እንዲሸሽጋችሁና እንዲጠብቃችሁ፣ እንዲሁም ሲያስፈልግ ከእናንተ ጋር እንዲሆን፣ ይህም የአውሬውን ምልክት ላለመቀበል ወይም ታዛዥ መሆናችሁን ለማሳየት ለሰውዬው ላለመስገድ፣ በዚህም ለመያዝ ወይም ለመደበቅ ወይም ለመሞት ስትወስኑ እንዲያጠነክራችሁ ነው፡፡ ይህ የሚሰገድለት ሰው ራሱን በምድር ላይ መሪ ብቻ ሳይሆን አድርጎ ያቀረበው እንደ አምላክም ጭምር ነው፡፡ አለምን ሁሉ የሚገዛውም በአንድ መንግስት ፣ በአንድ ሃይማኖትና በአንድ የገንዘብ መዋቅር ሥር በማድረግ ነው(ጌታ በዚህ ሥልጣን ላይ የሚቀመጠው አባማ እንደሆነ ጠቁሟል)፡፡

አሁን ምርጫው ግልፅ ነው፡፡ ይኸውም ህይወታችሁን ለእግዚአብሔር እጅ አሳልፋችሁ በመስጠት ሥጋችሁ ለሞት አሳልፋችሁ በመስጠት ለዘላለም ከእርሱ ጋር በመንግስተ ሰማይ መኖር፡፡ ወይም ለእነዚህ ጥቂት ለሆኑ ሰባት አመታት ለሥጋችሁ በመፍራት፣ ለሚመጣው መንግስትና ለሚመጡት ገዢዎች  መታዘዝና እነዚህ አመታት ባለቁ ጊዜ ነፍሳችሁን ለሰይጣን በመስጠት ስትሞቱ ወደ ገሃነም መውረድ፡፡

ለዘላለም በህይወት መኖር ከፈለጋችሁ በሥጋ ለመኖር ብላችሁ ለሰው ሁሉ ለመሸጥና ለመግዛት ተብሎ በሥራ ላይ የሚውለውን ምልክት አትቀበሉ፡፡

"የኔ ውድ ታውቂያለሽ መሪዎቹ በዚህ ምክንያት እንደሆነ ሳያገኙኝ የቀሩት? እነርሱ የውጪ ሁኔታዎችን ብቻ በመመልከት በህጉ ላይ አጅግ አተኩረዋል፡፡ ስለዚህም የህጉን የልብ ሐሳብ ሊያዩ አልቻሉም፡፡" እናም እነሱ የሚያስቡት በእድሜያቸው ሙሉ ህጉን ስለጠበቁ መንግስተ ሰማይ የሚገባቸው እንደሆነ ነው፡፡ ሴተኛ አዳሪዎች ከወንዶች ጋር በመተኛት ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን በስነ ምግባር ጉድለት ስለሚያገኙ በፍፁም መቼም ይቅርታ ይደረግላቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህም አንዳንዶች እንኳ ንስሐ ቢገቡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ይቅርታ አግኝተው ወዲያው  መንግስተ ሰማይ ይገባሉ የሚለው ሐሳብ የሚዋጥ አይደለም፡፡"

"እነሱ ያመለጣቸው ነገር እኔ ለማስታረቅ የከፈልኩት መስዋዕት ነው፡፡ ይህ የተደረገው መስዋዕት ደግሞ በበግ፣ በፍየል ወይም በእነርሱ መልካም ሥራ ሳይሆን በእኔ ደም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለእነርሱ አሰቃቂና ሊነገር የማይገባው ቆሻሻ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ዕርማት ነው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ያስቻለው፡፡ በዚህም የኔን ሥጋ መብላትና የኔን ደም መጠጣት የሚለው ሐሳብ ለእነርሱ ከሚገምቱት ሁሉ በላይ የመጨረሻ ጎጂና የማያስደስት ነው፡፡ ነገር ግን የኔ ደም በምህረት መቀመጫው ላይ ተቀምጦ ሲታይ ግራ ከመጋባት ወደ መደነቅ ነው የሚገቡት፡፡ አንዳንዶቹ ለቀልድ የተደረገ መስሏቸው ይገስፃሉ፡፡ አንዳንዶች እነዚህን ዓመታት ሁሉ ስሙን ስላጠፉ በፊታቸው ተደፍተው በፍፁም የልብ ስብራት በሐዘን ይመታሉ፡፡ አንዳንዶች ማየት ባለመቻላቸው፣ ጥቃት በመፈፀማቸውና ይህ አሁን የደረሱበት ነገር ስለረበሻቸው ካገነበሱበት ከዚያ ቦታ ለቀናት  አንዳንዶችም ለሳምንታት እንኳን መነሳት ያቅታቸዋል፡፡ በዚህም በጥልቅ ንስሐ ውስጥ ይገባሉ፡፡

" አዎ ህዝቤ ግትር ናቸው፡፡ ነገር ግን አንዴ እውነቱን ካወቁ ለእውነት ደግሞ ግትር ይሆናሉ፡፡ በዚህም ብዙዎች ስለ ስሜ ሲሉ ራሳቸውን በደስታ ለሞት አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡ ማረጋገጫ የላኩላቸው ስለምወዳቸውና አንዳንዶች ደግሞ ትጉዎች ስለሆኑ ነው፡፡ አዎን! በወጣቱ ልጅ በኩል፣ አዎን! አሁን እኔጋ በሚገኘው እጅግ በተከበረው በአይሁድ ሃይማኖት መሪ በኩል/ራባይ/፣ አዎን በታቦቱ በኩል፣ አዎን! አዎን!  በማያልቅ ማረጋገጫ አጥለቀልቃቸዋለሁ፡፡ በግራ መጋባታቸውና በአይነ ሰውርነታቸው ፋንታ የኔን መረዳት እልክላቸዋለሁ፡፡ በዚህም አይምሯቸው ይከፈታል፡፡  "

"ኦ! ህዝቤ ንስሐ ገብቶና 180 ዲግሪ ወደ እኔ ተመልሶ ማየት እንዴት ድንቅ ነው፣ እንዴትስ የሚያፅናና ነው፡፡ "የእነሱ በእውነተኛ ፀፀት ወደ እኔ መመለስ በእውነትም ክብር ያለው ነው፡፡ ከዚያም እኔ በምድር ለቀሩት የተውኩላቸውን ትምህርት እንዲሁም ብሉይ ኪዳንንና አዲስ ኪዳን በማገናኘት ብዙ አዳዲስ መገለጦችንና መረዳቶችን ለማስተማር ይነሳሉ፡፡

"እንዴት በክብር የተሞላ ጊዜ ነው የሚሆነው? ህልማቸው ሁሉ የሚፈፀምበት ጊዜ! በመጨረሻም የእነሱን መሺያኽ! /መሲህ/ ያገኛሉ፡፡"

# መልዕክት አራት
# ህፃናቶችና እንስሶች ሁሉ ምን ይሆናሉ?

{What happened to all the children and animals?}

ኢየሱስ እንዲህ አለን፡- ህፃናትና እንስሶችም ይወሰዳሉ፡፡ የሚወደዱትን እንዲሰቃዩ እዚህ አልተዋቸውም፡፡ ከእናንተ ጋር ይወሰዳሉ፡፡

"አዎ እንሰሳቶቻቸው አብረው እንደሚወሰዱ ለሁሉም መንገር ትችያለሽ ፡፡ ፈረሶች፣ ድመቶች፣ ውሾች፣ ወፎች - የሚወደዱና ለእናንተ ቤተሰብ የሆኑ ሁሉ፡፡ እንደገና አንድ ጊዜ ልናገር እነዚህን ድሆች አልተዋቸውም፡፡ ለእናንተ መፅናናት የነበሩ እነዚህ ንፁህ ፍጥረታት በዚህ በታሪክ አስከፊ ወቅት በፍፁም አልተዋቸውም፡፡"

"የሚወደዱና ለእናንተ ቤተሰብ የሆኑ" ሲል *ለማለት የፈለገው እንሰሶች ሁሉ ለእኛ እንደ ቤተሰብ በመሆናቸው ነው፡፡*

"ደግሜ ደጋግሜ ብዙ ጊዜ እንዲያገለግሏችሁ አድርጌያለሁ፡፡ ዓይናቸውን ስታዩ፣ ሲነኳችሁና፣ ሲጎነትሏችሁ፡፡ ስታቅፏቸውም ደስታን አግኝተዋል፡፡ ስለሚወዷችሁ ቸል ለመባልና ለስቃይ አልተዋቸውም፡፡"

"ደግሞም የልጅ ልጆቻችሁን አብሬ ከእናንተ ጋር እወስዳቸዋለሁ፡፡ አንዳንዶቻችሁ የልጅ ልጆቻችሁን የማየት መብት በልጆቻችሁ ተነፍጋችኋል፡፡ በዚህም የመገለል ስቃይ ደርሶባችኋል፡፡ እነዚህ ህፃናት ወደ መንግስተ ሰማይ የሚወሰዱበት ጊዜ ስለሆነ ለእናንተ የመጠገኛ ጊዜ ነው፡፡"

"ብዙ አገልጋዮቼ ስለ እንሰሳት ያለኝ ምህረት ምን ያህል እንደሆነ እውቀቱ የላቸውም፡፡ እንሰሶች በምድር ላይ ምን እውነተኛ ድርሻ እንደተጫወቱ አይገባቸውም፡፡ አዳም ከእንሰሶችም ጋር ህብረት ነበረው፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን ከእንሰሳት ጋር ቅርበት ቢኖረውም ሴቷን እስከፈጠርኩለት ድረስ ማንም ለእርሱ ተስማሚ የሆነ ጓደኛ አልተገኘለትም፡፡ "

“ቢሆንም ግን ባጠቃላይ ከእንሰሳትና ከለማዳ እንሰሳት ጋር ያላችሁን ግንኙነት ዝቅ አታድርጉት ፡፡ እኔ በፍቅር ነው የምወዳቸው፡፡ አንዲትም ድንቢጥ በመሬት ላይ አትወድቅም፡፡ ስለዚህም እኔ የማልቀበለውና ወደ መንግስተ ሰማይ መልሼ የማላመጣው የለም፡፡

"በመንግስተ ሰማይ ከእነር ጋር በነፃ ትግባባላችሁ፡፡ ይህም ጊዜ በአብዛኛው የፍቅርና የጨዋታ ጊዜ ነው፡፡ ከዶልፊኖች ጋር ትዋኛላችሁ፡፡ ከአንበሶች ጋር አብራችሁ ትወደወቃላችሁ፣ ከኦተሮች / otters /ጋር በፀጥታ ትጓዛላችሁ፣ ከፖላር ድብ ጋር ትንሳፈፋላችሁ፣ እንዲሁም በግዙፍ ግሪዜሊዞች/ grizzlies / መዳፍ ውስጥ ትሸጎጣላችሁ፡፡ በፍቅር እንኳን ደህና መጣችሁ ይሏችኋል፡፡ በመንግስተ ሰማ ሁሉ ነገር በፍቅር የተሞላ ነው፡፡ ንቦች እንኳን ለእናንተ አድናቆታቸውን ገልፃሉ፡፡"

## መልዕክት አምስት
## እነ እከሌ እኛ እዚህ ለመቆየት መርጠን የቀረነው ብለው ነግረውናል?

{So and so just told me that he chose to stay here?}

አንዳንዶቻችሁ እዚህ የቀራችሁበት ምክንያት ጌታን አጥብቃችሁ ባለመያዛችሁና ህይወታችሁን ሙሉ አሳልፋችሁ ስላልሰጣችሁ ነው፡፡ አላመናችሁም ደግሞም ለእርሱ አልኖራችሁም ነበር፡፡

አንዳንዶቻችሁ ደግሞ ምንም እንኳን ብዙ አደጋ ፣ ብዙ ፈተና፣ ብዙ መከራና ብዙ የማይመች ነገር ቢኖረውም ለዚህ ጊዜ ተመርጣችሁና ተጠርታችሁ ነው እዚህ የቆያችሁት፡፡ ለአዲስ ክርስቲያኖች ወይም ራሳችሁን በአዲስ መልክ ለጌታ ህይወታችሁን የሰጣችሁ፣ ይህ ጊዜ ከዘመናችሁ ሁሉ እጅግ አጓጊ ነገር ግን ደግሞ የመጨረሻ ትግል የበዛበት ጅማሪ ወቅት ነው፡፡ ቅሬታ ለመሆን የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ እድሜያችሁን ሙሉ ለጌታ በእሳት ውስጥ ለመኖር ስትጠብቁት የነበረ ጊዜ ነው፡፡ እናንተ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰችው ቤተ ክርስቲያን ቅሬታዎች ናችሁ፡፡ ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን፣ የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ (ራዕይ 12፡17)፡፡

እናንተ የተመረጣችሁት መሪ ለመሆን፣ ምሪት ለመስጠትና ከክፉ ጋር ለመዋጋት ነው፡፡ እናንተ እራሳቸውን ለጌታ ስላልሰጡ ወደ ኋላ ከቀሩት ወገን አይደላችሁም፡፡ በፍፁም ፣ እናንተ ለዚህ ጊዜ ተመረጣችሁ የተጠራችሁ ቅሬታዎች ናችሁ፡፡

አንዳንዶቻችሁ ተዋጊዎችና ለእንደዚህ ዓይነት ጊዜ የተፈጠራችሁ ናችሁ፡፡ አገሩቱን/አሜሪካን/ መልሶ ለማቋቋም ለውጊያ የተመረጣችሁ እናንተ ጌታ ከእናንተ ጋር እንደሆነ እንድታውቁ ይፈልጋል፡፡ እየተዋጋችሁ ያላችሁት ለብቻችሁ አይደለም፡፡ የእርሱ ክንድ ጠንካራና ኃያል ነው፡፡ በዚህም ኃያል ክንዱ እናንተን ከጠላት መከላከል ብቻ ሳይሆን እርሱ የሚፈልገው ጠላትና ግራ በማጋባት እንድታሸንፉት ጭምር ነው፡፡ ሁሉንም ውጊያችሁን በፀሎት ጀምራችሁ በምስጋና ጨርሱት፡፡ እግዚአብሔር በእናንተ ይህችን አገር /አሜሪካን/ ከአመድ አንስቶ ወደ ፅድቅ ይመልሳታል፡፡

ማንም ታናሽ አድርጎ እንዲቆጥራችሁ አትፍቀዱ፡፡ እናንተ ቸልተኛ ሆናችሁ ሳይሆን ለፅድቅ ለመዋጋት በእርሱ የተመረጣችሁ ከዛም በበለጠ ለኢየሱስ ምስክር ለመሆን ራሳችሁን ለሞት እንኳን አሳልፋችሁ የምትሰጡ ናችሁ፡፡ ጎበዝ ሁኑ፡፡ማንም ዝቅ አያድርጋችሁ፡፡ የጠላትን ወሬ ፍፁም እንዳትሰሙ፡፡ ምክንያቱም እርሱ በውሸቱ እናንተን በማሰቃየት ተስፋ ለማስቆረጥ መሞከሩ አይቀርም፡፡ ነገር ግን ጌታ ከእናንተ ጋር ስለሆነ በጌታ ጠንክራችሁ ቁሙ፡፡

ሌላ የምነግራችሁ አንድ ነገር በመንፈስ ቅዱስ መፀለይ ተመራጭነት ያለው የጦር መሳሪ መሆኑን ነው፡፡ የዚህም ማረጋገጫው በልሳን መናገር መቻል ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ስትፀልዩ በእግዚአብሔር መንፈስ ቋንቋ ትናገራላችሁ፡፡ በዚህም በወቅቱ ያላችሁበትን ሁኔታ የሚመለከተውንና የሚያስፈልገውን ትክክለኛ ፀሎት መፀለይ ትችላላችሁ፡፡ ጠላት ስለዚህ ስጦታ እንዲዋሻችሁ ከአሁን ወዲያ አትፍቀዱለት፡፡ በልሳን መናገር ኃይል ስላለው ነው እርሱ የሚጠላውና የሚያናንቀው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን ፀሎት ነው በእናንተን አልፎ የሚፀልየው፡፡

እስካሁን በመንፈስ ቅዱስ ካልጠመቃችሁ ማድረግ ያለባችሁ አንድ ነገር መጠየቅ ብቻ ነው፡፡ ይህንን ለመጀመር ጥሩው ዘዴ በዝማሬና በአምልኮ ሆናችሁ መንፈስ ቅዱስ አደበታችሁን እንዲቆጣጠር መፍቀድ ነው፡፡ ከዚህም ቅባት ጋር ብዙ ብዙ

# መልዕክት ሃያ አራት
# አሁን ለአለም ያላቸውን ፍቅር መተው አለባቸው

{They must forget now their love affairs with the world}

"አንድ መሬት ከተናደ በኋላ  መሬቱ ምን ያህል ውፍረት እንደነበረው ምንም አይታሰብም፡፡ የሚታሰው በጥፋቱ ምክንያት የመጣው ጉዳት ብቻ ነው፡፡ ያን ጊዜ ታዲያ በፍርስራሹ መካከልም ሆነው ይፈልጉኛል፡፡ አለምን መውደዳቸው እንዴት ራቁታቸውን እንዳስቀራቸውና በችግር ውስጥ እንደጣላቸው ይገነዘባሉ፡፡ በአገኙኝም ጊዜ እጄን ዘርግቼ እቀበላቸዋለሁ፡፡ በቁስላቸውም ላይ ዘይትን አፈስሼ በቅድስና ወደላይ አነሳቸዋለሁ፡፡

"ለማለት የፈለኩት ከንጥቀት ወደ ኋላ ለቀሩት ማዘን የለባችሁም፡፡ የለም ማዘን የለባችሁም፡፡ ይህ የነሱ እጣ ፈንታ ነው፡፡ ምክንያቱም እነሱ ከእኔ ተለይተው በራሳቸው ሁሉን ነገር በማድረግ ለመኖር መርጠውና ህይወታቸውን ሁሉ ትኩረት አድርገውት የነበረው ስኬታማ ለመሆን ስለነበረ ነው፡፡ አዎ ይህንን ነበር የመረጡት፡፡ አለምም እንዲህ በመሆኗ አይነስውርና ራቁት አድርጋ በፊቴ አስቀረቻቸው፡፡ ይህንንም የፈቀድኩት ነፍሳቸው እንዲድን ነው፡፡ ያለዚህ ግን ገሃነም እየሞላ ነው፡፡ ሁሉም መጥፎ ሰዎች ሆነው አይደለም፡፡ አምላክ የማያስፈልጋቸው አምላክ የለሾች ሆነው እንጂ፡፡ የኔ ምህረት ነው የእነሱ አለም ተጨፍልቆ እንዲያበቃ ያደረገው፡፡ የኔ ፍቅር ነው እንደዚህ ዓይነቱን መቅሰፍት ያመጣው፡፡ ባዶ መቅረታቸውና እውነተኛ የመፅናናት ረሃብ ብቻ ነው ወደእኔ የሚያመጣቸው፡፡

"አያችሁ ሰው አንዴ ቤቱን በአሸዋ ላይ ከሰራ ዝራብ ይመጣና ቤቱ በጎርፍ ይወሰዳል፡፡ በዚያን ጊዜ ያ ሰው ቤቱን በድንጋይ ላይ መስራት እንዳለበት አስፈላጊ መሆኑን ይረዳል፡፡ ታዲያ ያን ጊዜ እኔ ላስተምረው ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ ስለዚህ አያችሁ ሊመጣ ያለው ነገር መቅረት የማይችለው ምክንያት ልጆቼን በእውነትና በመንፈስ ወደ እኔ ለመመለስ ያዘጋጀሁት መንገድ ስለሆነ ነው፡፡

"አዎ ከባድ ነው፡፡ አዎ ጭካኔ የተሞላበት ነው፡፡ አዎ ሲመለከቱት ትክክል ያልሆነ ሊመስል ይችላል፡፡ ይህ ግን ለአንድ ታዳጊ ህፃን ልጁ ቅንጡ መኪና ለመግዛት ወይም ቅንጡ ቤት ለመስራት የድሃ አገሮችን ለመበዝበዝ ሥራ ለበዛበት ለአንድም ሰው አልተባለም፡፡ በዚህ አመለካከት ለተቀረፁ ሰዎች ዋናው ተፈላጊው ነገር የሚፈልጉትን ማግኘታቸው ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህ የደሃ አገሮች ያሳለፉትን እውነተኛ የህይወት ገጠመኝ እነርሱም ይቀምሱታል፡፡ እናንተ ስትመለከቷቸው ትህትና የሚያበዙና የሚቅለሰለሱ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው የሚመስሏችሁ እነርሱ ግን ተስፋ በሌለው  ባህልና ኢኮኖሚ የሚኖሩ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ግን እናንተ በመበልፀግ ላይ ናችሁ፡፡

"ክሌር ይህ በጣም በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ እናንተ የማታዩት ነገር እነዚህ ሰዎች እንዴት እየተበዘበዙ እንዳሉ ነው፡፡ ለመሆኑ እኔ ለሚዘራ ዘርን እንዲሁ አልሰጠሁምን? ነገር ግን እነዚህ ስግብግብና ክፉ ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም የሚጠቅም እቅድን በማውጣት ደሃውን በማስገደድ ዘርን ከእነርሱ ላይ እንዲገዛ ያደርጋሉ፡፡ ይህንን እስከ መቼ ልፍቀድ፡፡ በየቀኑ የደሃው ጩኸት ወደ ጆሮዬ ይደርሳል፡፡ ለህክምና እንኳን የሚያስፈልጋቸውን በማጣት ይሰቃያሉ፡፡ በአንፃሩ በእናንተ አገር (በአሜሪካ) መካከለኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንኳን ህክምና በደንብ ተመስርቷል፡፡ ከዚህም በበለጠ ሁኔታ አዲስና የተሸሻለ ለማድረግ እንዲሁም በበለጠ ለመቆጣጠርና የበለጠ አትራፊ ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ ምንም የማያውቁትን በመበደል ነው፡፡

"ኦ! ይህ ከምክንያቶች ሁሉ ያለፈ እጅግ የተበላሸ ነገር ነው፡፡ አባቴ ይህ እንዲቀጥል ለአንድ ደቂቃ እንኳን ለምን ይፍቀድ? እኛ የሰዎችን ልብ ለመቀየር ብዙ ጥረት አድርገናል፡፡ ነገር ግን ከሁሉ በልጦ ለመገኘትና ለአለም ቅንጦት ያላቸው ከልክ ያለፈ ፍላጎት ዓናቸውን ፍፁም አሳውሮ ትክክል ላልሆነ የህይወት አኗኗር ዳርጓቸዋል፡፡

"በተለመደው ሁኔታ ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ለአንቺ አውርቼ አላውቅም፡፡ ነገር ግን እንድትረጂ የምፈልገው የብልሽት መልኮችን ነው፡፡ በየቀኑ የማያቸው ነገሮች እጅግ የሚደንቁና የፍትህ ያለህ በማለት የሚያስጮሁ ናቸው፡፡ ከዚህ የባሰው ነገር ደግሞ ይህ ደሃውን እየጨመቁ ምንም ሳንቲም እንዳኖረው የሚያደርጉት የተቀነባበረ ባህላዊ ወንጀል የእያንዳንዱን ሰው መሰረታዊ ህይወት እያጠፋ መሆኑን ያለማየታቸው ነው፡፡

"ይህ አንዱ ገፅታ ብቻ ቢሆንም እንኳን ጥላቻን፣ ያለመረጋጋትንና ተስፋ መቁረጥን ያነሳሳል፡፡ ሙስሊሞች ለእምነታቸው ራሳችውን መስዋዕት አድርገው የሚሰጡበት የራሳቸው ምክንያት አላቸው፡፡ ይህም በዚህ በተጣመመ፣ በተበላሸና ተስፋ በሚያስቆርጥ አለም ውስጥ ደስታን ሊሰጣቸው የሚችል አንድ ነገር እርሱ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ለምክንያት መኖር አንድ የሚፈልጉትን ነገር የማጣት ህመምን ይሸፍናል፡፡ ለመኖር ምክንያት ሲጠፋ ግን በክብር መሞት ለክብር ያለውን ስሜት እንዲመልስለት ያደርጋል፡፡ በፍትህ ማጣት ምክንያት ሰው በዚህ ምድር ማግኘት ያልቻለውንና ያጣውን ነገር ሰይጣን 'በመንግስተ ሰማይ' እሰጣለሁ በማለት ሰዎች ራሳቸውን ከዚህ ምድር ራሳቸውን እንዲያጠፉ ያደርጋል፡፡ ታዲያ እነዚህ ሰዎች ድሆችን የሚያሳድዱትን የባንክ ባለቤቶችንና የአለም መሪዎችን እንዴት አይጠሉም? እነዚህም አብዛኛዎቹ አይሁዶች የናቸው፡፡

"ከዚህ በተጨማሪ ሌላ ስሜት ደግሞ አለ፡፡ ሥራን የማጠናቀቅ ስሜት፡፡ ይህም 'ሴተኛ አዳሪዋን አጥፋ' የሚል ነው፡፡ ይህ እራሱ ክብር ያለው ነው፡፡ ስለዚህ አያችሁ? ይህ ችግር ተስፋ የሌለው የተወሳሰበ ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ለመንገስና ለመግዛት ስመጣ የብረት በትሩ የሚሰርቁትንና የሚያዳሉትን በጣም ዝቅ ካለ ሰው ላይ እንኳን ይሰብራል፡፡

"ፍትህና ክብር ለሚፈልጉት ሁሉ ይኖራል፡፡ በክብር ለመኖር የሚያስችል እውነተኛ ሙያዊና አስፈላጊ የትምህርት እድል ለሁሉም ይሰጣል፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ማንም ካለ እግዚአብሔር መበልፀግ አይችልም፡፡ ማንም አይችልም፡፡ በመጀመሪያውንም ጠንካራ የሆነ ለእኔ መሰጠትና እኔን ማገልገል መፈለግ ከሌለ ማንም በህይወት ሊኖረው አይችልም፡፡ ማገናዘብ የማይችሉ ካልሆኑ በቀር እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ውስጥ መኖር አስፈላጊነቱን ያያል፡፡

## መልዕክት ሃያ ሰባት
## የመከራው ዘመን ካለፈ በኋላ ምን እንጠብቅ?

{What you have to look forward to once the tribulation is over}

በዚህ ጥራዝ ኢየሱስ ስለ ሰማይ የተናገረውን መልዕክቶች ሁሉ ከማጠቃለል ልናደርግ የፈለግነው ሰማያትን ለማሳያ የሚጠቅመንን ብቻ ይሆናል፡፡ ይህም መንግስተ ሰማይ ምን እንደሆነ፣ በእዛ ምን እንደምናገኝ ፣ በእዛ ነገሮች እንዴት እንደሚሰሩ፣ ክርስቶስ እንዴት እንደሚያያችሁ፣ በቀጣዩ ዘመናት ምን እንደምናረግ /እንደምናይ/ ፣ የመከራው ዘመን ካለፈና ምድር ከታደሰች በኋላ የአንድ ሺህ አመቱ የኢየሱስ አገዛዝ (ሚሊኒየም የተባለው) ናቸው፡፡ የእኛ ፍላጎት ከተሰጠው ተስፋ የተነሳ የመከራውን ዘመን ፀንታችሁ እንድታልፉ ነው፡፡ ይህም ተስፋ የዘላለም ቤታችሁና ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም አብራችሁ የምታሳልፉት ህይወት ነው፡፡ ከመጀመሪያው ትምህርት ጋር ተያያዥ የሆነ ማጣቀሻ ይኖረዋል፡፡ ይህም ሁሉንም መልዕክት ለማንበብ ከፈለጋችሁ ጥቅሶችይረዷችኋል፡፡ መልዕክቱ በመጀመሪያ የተሰጠው ለሙሽራው ነው፡፡ ነገር ግን የሰማዩ አስደናቂነትና ክብር ተመሳሳይ ነው፡፡

ጌታ በመከራው ዘመን ሁሉ ከእርሱ ጋር እንድትጣበቁ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ክብር ለሚሆነው ነገር ሁሉ መፅናት እንድትችሉ፣ ጥንካሬና ብርታትና እንዲጨምርላችሁ በተስፋ ይባርካችሁ፡፡ በጣም በቀረባችሁት ቁጥር ከእርሱ ጋር በእምነት፣ በመታመንና በመታዘዝ በቅርበት ትረመዳላችው፡፡ እንዲሁም ካላችሁበት ጊዜ ይልቅ የሚመጣው ቤታችሁ እውነት ሆኖ ይሰማችኋል፡፡ ይህ የምታነቡት ነገርም ተዘጋጅቶ ለእናንተ የተቀመጠ ነው፡፡ ይህም በጌታችንና ባአዳኛችን በእየሱስ ክርስቶስ፣ በአባታችን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በደስታ ለዘላለም ለመኖር ነው፡፡

### ልባችሁ የእርሱ ዙፋን ነው

{Your Heart is His throne}

እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ይኖራል፡፡ በእኛ ውስጥ! እርሱ ውጪ ሳይሆን ያለው በእኛ ውስጥ እንጂ፡፡ ይህ ሌላ ወርድና ስፋት/Dimension/ ነው። ወደ አንድ ትንሽ ሚስጥር ልወስዳችሁ ነው፡፡ እግዚአብሔር ባለበት ሁሉ ሰማይ አለ፡፡ ስለዚህም ወደ ልባችው ውስጥ ስትገቡ የጌታ ልብ ውስጥም ገባችሁ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ልባችው የእርሱ ዙፋን ስለሆነ ነው፡፡ በልባችው ውስጥ ልክ ንጉሥ በዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ ሁሉ ይቀመጣል፡፡ ወደ ዙፋኑ ፀጥ ባለ ፀሎትና በማደናነቅ ስትገቡ እግዚአብሔር የመገኘቱን ምልክቶች ይገልጣል፡፡ የምታዩትም በውጪ በኩል ነው፡፡ እንደዚህ የሚያደርገውም እኛ ማየት የለመድነው ውጪ የሆነን ነገር ስለሆነ ነው፡፡

### ኢየሱስ ወደ መንግስተ ሰማይ የመግቢያ በር ነው

{Jesus is the door to Heaven}

በክርስቶስ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ እግዚአብሔር አብ ማንም መግባት አይችልም( ዮሐንስ 14-6)፡፡ ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እርሱ ወደ አማረው ሥፍራ ወደ መንግሰተ ሰማይ መግቢያ በር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአለም

ላይ የሚገኙ ብዙ ክርስቲያኖች መንግስተ ሰማይ ምን ዓነት እንደሆነች እየተለማመዱዋት ነው፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ሚስጥራትን እየገለጠላቸው ነው፡፡ የሚመስለው ልክ ዳመናት ተከፍለው የሌላ ወርድና ስፋት በር /dimension has opened/ ለክርስትና ተከፍቶ በውስጡ በማለፍ ብዙ የሚያማምሩ ነገሮችን እያየን እንደሆነ ነው፡፡

## ኢየሱስን በመንግስተ ሰማያት መገናኘት

{Joining Jesus in Heaven – a Chronicle}

እኔ እንዲህ በማለት ጀመርኩ . . .  ይህ ደግሞ አዲስ የፀሎት ወቅት፣ የለውጥ ጊዜ ነው፡፡ እናም እየወደድኩት ነው፡፡ በድጋሜ በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ይህንን ከሰዓት በኋላ እየተራመድን ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር አብ የዛፍ ቤት እየተጠጋንና  በተስተካከለ ነጭ አሸዋ ላይ ያለውን ተራራ እየወረድን ነው፡፡ በነገራችን ላይ በመሬት ላይ የሚገኝ ነጭ አሸዋ እወዳለሁ፡፡ ኢየሱስ በተራራው ጉዞዋችን መኃል ላይ ቆም ብሎ እናቱ የሰራችልንን የብርድ ልብስ ዘረጋ፡፡ ብርድ ልብሱ ቀይ ትልቅ ልብ ቅርፅ በላዩ ላይ ተጠልፎበታል፡፡ አብረን እየበላን እንድንደሰት የሰርጌን ኮኪስ እና የሚጠጣውን ጣፋጭ እንዳወጣ አስታወሰኝ፡፡ አ! እንዲህ በማድረጋችን እንዴት ደስ እንዳለኝ!

በደስታ አብረን ተመገብን፡፡ ነገር ግን እኔ የተራረፉ ምግቦችን ከአካባቢያችን ምግብ ማከማቻ እየወሰድኩ ለድሆች የማከፋፍለው ሥራዬ ትዝ ብሎኝ ሐሳቤ ተሰረቀ፡፡ ድሆች ስላችሁ በካርቶን ሳጥን ውስጥ የሚኖሩ ፤የተቃጠለ መኪና ውስጥ የሚያድሩ ህፃናቶች ናቸው፡፡ በጣም በጣም ድሆች ናቸው፡፡ እናም ብዙዋቹ የወጡት በጣም ከተጎዱ ሱሰኛ ቤተሰቦች ነው፡፡ ታውቃላችሁ ቤተሰቦቻቸው የሱስ እፅ ሥራ ላይ ለረዥም ጊዜ ተሰማርተው የነበሩ ናቸው፡፡

ታዲያ ሁልጊዜ ሐሙስ ሐሙስ ምግቦችን ከምግብ ማከማቻዎች ሰብስበን እንወስድላቸዋለን፡፡ እናም ዛሬ ምግቡን ለመውሰድ እዛ መገኘት ነበረብኝ፡፡ እዛ መገኘት ያለብኝ የተወሰነ ሰዓት አለ፡፡ ኢየሱስም ያሳሰበኝ ነገር ስለገባው «እጠብቅሻለሁ» አለኝ፡፡ ስለዚህ ወጥቼ ማድረግ ያለብኝን ጨርሼ ስመለስ ካቆምንበት እንደምንቀጥል እየጠበኩ ነበር የመጣሁት፡፡

ኦ የእኔ ደስታ! ትቼው የሄድኩበት እዛው ደን ውስጥ እየጠበቀኝ ነበር፡፡ መብላት እንደጨረስን «ነይ»  በማለት እጄን ያዘኝና ያንን ተራራ በቀላሉ ወረድነው፡፡ በመንግስተ ሰማይ ሚዛናችሁን ያለመጠበቅ ያለው አጋጣሚ እጅግ ጥቂት ነው፡፡ ጠንካራ ድንጋዮች የሉም፡፡ ድንገት በመደንገጥ "ወይኔ" የሚባል ነገር የለም፡፡ እያንዳንዱ ፍጥረት እስከ ጥግ ይታዘዛል፡፡ አበቦችን ለማንሳት ስትፈልጉ በእጆቻችሁ ላይ መጥተው ያርፋሉ፡፡ ስታልፉ አክብሮት ያሳያሉ በእውነት ራሳቸውን ያዘሩና ከጭንቅላታቸው ዝቅ ይላሉ፡፡ ንቦች የማር ቀፎአቸው ውስጥ እንድትገቡ ይፈቅዳሉ፣ የልብ ቅርፅም እየሰሩ ይበራሉ፡፡ ባላጩት ድንጋይ ስትነኩት ቀላልና ለስላሳ ይሆናል፡፡

ተራራው ሥር ስንደርስ ኢየሱስ በድንገት ወደ ቀኝ ዞር እናም በፍለፊቴ አሥራ ሁለት ጫማ ርዝመት ያለው ግማሽ ክብ የሆነ ዋሻ ተመለከትኩ ፡፡ በመጀመሪያ ውስጡ እንደ ሌሎቹ ዋሻዎች ሁሉ ጨለማ መስሎኝ ነበር፡፡ ነገር ግን በመንግስተ ሰማይ እንደዛ አይደሉም፡፡ እዚህ ከሁሉም ፍጥረት ውስጥ ብርሃን ያንፀባርቃል፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ሁሉን አንድ ላይ እንደያዘ

ይህ ግልፅ ማረጋገጫ ነው

ወደ ውስጥ ስንገባ የዋሻው ጣራ በደማቅ ሰማያዊ የተሰመረ የሚመስል፣ ጥርት ያለ ምንጣፍ  በሚመስል የተነጠፈ፣ ልክ እንደ ቀጭን አልጌ ነገር ግን ከእርሱ ይልቅ ከትናንሽ ሰማያዊ የከበረ ድንጋይ የተሰሩና ለመመልከት በቂ ብርሃን ያለው ነው፡፡ በልጅነቴ ድንጋይ ስለቅም በነበረ ጊዜ እንደነበሩ አይነት መሆናቸውን አስታወስኩ፡፡ አይኔን ካስተካከልኩ በኋላ ትንሽዬ ወራጅ ውኃ ስፋቱ ከ 10 ጫማ እና ጥልቀቱ ከ 5 ወይም 6 ጫማ የማይበልጥ ተመለከትኩ ፡፡ ጥርት ያለ ንፁህና ታቹ ነጭ አሸዋ ያለው ነበር፡፡ የዋሻው ከፍታ 12 ጫማ አካባቢ መሆን አለበት፡፡ የውኃው ማፅባረቅ የብርሃን ሞገድ በመፍጠር ለዋሻው ድምቀትና ውበት ፈጥሮለታል፡፡

እዛ ስንደርስ ትንሽ ታንኳ እየጠበቀን ነበር፡፡ ኢየሱስ ከኋላ በመቀመጥ በዋሻው ውስጥ ይመራን ጀመር፡፡ በመጀመሪያው መዞሪያ ብዙ ለእኔ የሚያስገርሙ እና የሚያስደንቁ ነገሮች ነበሩ፡፡ በጣም ትልቅ፣ ውስጡ የሚያስተላልፍ እምነበረድ ቁመቱ ከ 3 እስከ 7 ጫማ የሚሆንና ብዙ አይነት ቀለሞችን የያዘ ነበር፡፡ይኸውም ወይን ጠጅ፣ ሰማያዊ፣ ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጎዴ ቀለሞች ያለው ነበር፡፡ በዚያም ጊዜ 'እንደ ኢሜራልድስ /emeralds/ የከበረ ድንጋይ አንድ ዓይነት ውዕድ ያለው ይሆን? እያልኩ በጭንቅላቴ እያሰብኩ እያለሁ በዋሻው ጎን በኩል የከበሩ ድንጋዮችን ማስቀመጫ ከውስጥ በኩል ወጣ፡፡ ማስቀመጫውም የተሞላው በሁሉም ዓይነት አንፀባራቂ አረንጓዴ ትንንሽ ኢሜራልድዎችና/emeralds/ በህይወቴ በምድር አይቼ የማላውቃቸው የቀለም ብዛት ያላቸው የከበሩ ድንጋዮች ነበር፡፡ አንድ እኔ በጣም የምወደው ቀለም ጠቆር ያለ ሰማያዊ /Azurite/ ትዝ አለኝ፡፡ ልክ ይህንን እያሰብኩ እያለ ዋሻው ሁሉ በሚያምር በሰማያዊ ትንንሽ ቀዳዳዎች ተሞላ፡፡ ትንንሽ ሰማያዊ አንፀባራቂ የከበሩ ድንጋዬች ተሞላ! ኦ! እንዴት እጅግ የሚያስደነቅ ነው!

አንዱን እምነበረድ ለመንካት እጄን ዘርግቼ መዳፌ ሲያርፍበት ተርገበገበ፡፡ የሚሰማችሁ ስሜት እጃችሁን የእስፒከር ሳጥን ላይ ስታስቀምጡ እንዳለው ዓይነት ነው፡፡ ከዚያም የማንጎራጎር ድምፅ ሰማሁ፡፡ በምድር ላይ ሆኜ ራሱን ድምጽ እያልኩት ወደ ኤሌክትሮኒክ ቅላጼ ተለወጠ፡፡ ማንጎራጎሩ በB ቅላፄ ነበር፡፡ ከዚያ ሌላው የድምፅ መስመር ደግሞ በE ቅላፄ ከዛም በC ቅላፃ!! ይህ ለእኔ እንዴት አስደሳች ነበር፡፡ በዛን ጊዜ የምሰማ የመሰለኝ የሚጮህ ድንጋይ ዓይነት ነበር፡፡

ኢየሱስ ከእርሱ ፊት ለፊት መቀመጫ አዘጋጀልኝ፡፡ ይህም እኔን ለመያዝና በጀርባዬ እርሱን እንድደገፍ የሚመች ነበር፡፡ ይህንን አስደናቂ ፍጥረት ሁሉ ስመለከት ይህንን ቦታ "የሚዘምረው ወንዝ" አልኩት፡፡ ነገር ግን ትክክለኛ ስሙ ይህ ይሁን አይሁን አላውቅም፡፡ ነገር ግን ደግሞ "ገነት" የሚለው በአይምሮዬ እንደገና መጣ፡፡ ይህም ከሠርጉ መዝሙር አንዱ ስንኝ እንዲህ ይላል «ካንተ ጋር መሆን በገነት መሆን ነው፡፡»

ተነስቼ መቀመጥ እስከማልችል ድረስ በሚያስደንቀው ዕረፍቱ ውስጥ መግባት ጀመርኩ፡፡ በክንዶቹ ውስጥ እንደተኛሁና በሚዘምረው ወንዝ ላይ እየተንሳፈፍን በቤታችን ወዳለው አልጋ የሚወስደኝን መንገድ አገኘውት፡፡ እሱም እንዲህ አለኝ . . . «እባክሽ ስለዚህ ቦታ ንገሪያቸው፡፡ ይህንን የፈጠርኩት ለእነሱ ደስታ መሆኑንና በቅርብ ቀን በተመሳሳይ ታንኳ ወደ መንግስተ ሰማያት ጥልቅ ስፍራ እንደምወስዳቸውና ውኃዎችም በደስታ ከእነርሱ ጋር እንደሚዘምሩም ንገሪያቸው፡፡»

በግምት ከሁለት ሰዓታት በኋላ ታድሼና  ማታ አብረን ለምንሰራው ስራ ተዘጋጅቼ ወደ ራሴ ተመለስኩ፡፡ እስካሁን የሠርጋችንን መዝሙር እየሰራን ነው፡፡

ኦ ጌታ ሆይ በጣም ድንቅ ስሜት እየተሰማኝ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ቀናት ድንቅ ነበሩ፡፡ በአንተ አስደሳች መገኘት ውስጥ ራሴን ነፃ ማድረግና አንተ ወደምትፈልግበት ቦታ እንድትወስደኝ ለመፍቀድ ትንሽ ቆይቼ ነበር፡፡ ስለዚህ አስደናቂ ስጦታህ አመሰግናለሁ፡፡ ደግሞም እባክህ እባክህ ሌሎችንም ወደዚህ ጣፋጭ ወደሆነ ቦታ እንድመራቸው እርዳኝ፡፡

እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰልኝ. . . «እሱ ነው ሐሳቤ» በተደሰተ ፊትና አይኖቹን ጭፍን ግልጥ እያረገ፡፡ «አለም ማን እደሆንኩና ባጠቃላይ ስለመንግስተ ሰማያት ምንም እውቀት የለውም፡፡ የሰው ልጅ በተሳሳተ አይነት ነው እኔን የሳለኝ፡፡ ራሴን እንኳን እነሱ በሳሉት ውስጥ መለየት እስከማልችል ድረስ ተሳስተዋል፡፡ አዎ አንዳንዶች እኔን በደንብ ገልጠውኛል፡፡ ነገር ግን እጅግ ጥቂቶችና ናቸው፡፡ በእውነት ለመናገር ሰው መሆኔን ምንም ገና አልነኩትም፡፡ ተጨዋች መሆኔን፣ የፍቅሬን ውበት፣ እናም በመንግስተ ሰማያት ከነሱ ጋር ስሆን በእውነት ደስ የሚለኝን ደስታ አላዩትም፡፡ ኦ የኔ ውድ እባክሽ ንገሪያቸው ደግመሽ ደጋግመሽ ንገሪያቸው፡፡ ለእያንዳንዱ የተለያየ ቦታ ለማዘጋጀት ነው የሄድኩት ፡፡ ለእያንዳዳችሁ ከሠራሁት አንዱም ድጋሜ ወይም ተመሳሳይነት የለውም፡፡ ልክ የኔ ቆንጆ ሙሽራ በፍላጎቷና በምርጫዋ የተለያየች እንደሆነች ሁሉ እንደ ፍላጎቷና እንደ ምርጫዋ ያማረን ቦታ አዘጋጂቼላታለሁ»

ኦ ጌታ ሆይ ልቤ በደስታ ትዘላለች፣ ነገር ግን ማን ያምነኛል?

«ምንም አትጨነቂ ዝም ብለሽ ንገሪያቸው፡፡ የማረጋገጪያ ምልክቶች ይኖራሉ፡፡ አንቺ ብቻ ዝም ብለሽ ንገሪያቸው፡፡ በጣም እንደምወዳቸው፤ ህይወቱን ለሰጠኝ ሁሉ በዛው ቀን እኔ አሳምነዋለሁ፡፡ አሁን ለሚቀበሉኝ ለእነርሱ ግን አይናቸውን ጨፍነው ወደ ዕረፍቴ መግባት ብቻ ነው፡፡ እናም ወደ አዘጋጀሁላቸውና ትልቅ ደስታ ወዳለበት በጥንቃቄ ተሸክሜ እወስዳቸዋለሁ፡፡

«ብቻ እመኑ»

# መልዕክት ሃያ ዘጠኝ
# በመንግስተ ሰማይ ጨዋታ አለ!

{There is fun in heaven!}

ይህ ጉዞ በቅርቡ የተደረገ ጉዞ ነው፡፡ እንዲህ በማለት እጀምራለሁ . . . እንደወትሮው እየደነስን ነበር፡፡ እኔ ብዙ ጊዜ ሳየው ከእኔ ጋር እየደነሰ ነው የማየው፡፡ ምክንያቱም እኔ የምስጋናና የአምልኮ መዝሙር ስለምከፍት ነው፡፡ እንዲህም አልኩት ኦ! ጌታ መደነስ ታውቅበታለህ፡፡ ዋው! ደስ የሚል ነው፡፡ በወቅቱም የለበስኩት ልብስ በጣም ቆንጆ ነበር፡፡ በሆነ ምክንያት ብቻ ከእርሱ ጋር ስሆን እንድለብስ የሚያደርገኝ የተለያየ ልብስ ነው፡፡ የዛሬው ደግሞ ልዩ ነበር፡፡ ልብሱም ሽፎን ሲሆን ስድስት ኢንች ስፋት ያለውና እንደ ደረጃ አንዱ በአንዱ ላይ የተደራረበ ነው፡፡ ቁመቱም በወለሉ ላይ የሚጎተት ነበር፡፡ በእውነት እጅግ ውብ ልብስ ነው፡፡ የልብሱ ቀለም ግራጫ ሮዝ ሲሆን በጀርባውም በሪቫን የታሰረ ነው፡፡  ፀጉሬም ወደኋላ ታስሮ ከርል ተደርጓል፡፡ ደግሞም ቲያራ አድርጌያለሁ፡፡ ግርማ ሞገስ የተላበሰ ዓይነት ዳንስ ደነስን፡፡ በምስጋናና በአምልኮ የተሞላ መዝሙር ስለመጣ ጌታ ቀስ ባለ መልኩ ነገር ግን ችሎታ በተሞላበት ሲደንስ አስደነቀኝ፡፡

እኔም . . . ጌታ አንተ ነህ? አልኩት፡፡ እናም አስደናቂና የሚያበራ ፊቱን ፈገግ ሲል በጣም ጥርት ባለ መልኩ አየሁት፡፡ በዚህ ጊዜ መዝሙሩን እንድዘጋው ጠየቀኝና ወደ በረንዳው ወጣን፡፡ ያለነው በፅጌሬዳ መናፈሻ ውስጥ ሲሆን ግዜው ምሽት ነበር፡፡ ስለ ምሽቱ ነገር በኋላ አብራራላችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም ምሽት በመንግስተ ሰማያት ስለሌለ ነው፡፡

እንዲህ በማለት ጀመረ . . . «መደነስ እንደምወድ ታውቂያለሽ»

«አዎ ግን አንተ ግራማዊና ሞገስ ያለህ፣ ደግሞም ተሰጥዎና ብቃት ያለህ ነህ!!»

እንዲህ በማለት መለሰልኝ «ከእግዚአብሔር ምን ትጠብቂያለሽ? ምንም ነገር ፍፁም ከሆነ ያነሰ ትጠብቂያለሽ?»

በዚህ ጊዜ ሳቅኩና  «ዋው ማንም ይህንን ንግግር ካንተ ከኢየሱስ የወጣ መሆኑን አያምንም»

«ጥሩ ለራሳቸው ነው የሚጎድልባቸው፡፡» እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . « አንቺ ምን ታስቢያለሽ? በጭቃ ውስጥ ያለሁ በትር ወይንስ ከክብሬ ታላቅነት የተነሳ ከሙሽራዬ ጋር መጫወት የማልወድ? እንዲህ አይደለሁም፡፡ እናም ሙሽራዬ ምን እንደሚገጥማት ማወቅ አለባት፡፡ ምክንያቱም እንደንሳለን፡፡ ስለዚህም ይህንን መልመድ አለባት፡፡ በማለት ፈገግ አለ»

«ኦ ጌታዬ አንተ በጨዋታ የተሞላህ ነህ፡፡ እናም ሰዎች ኃይማኖተኛ በመሆን ተጫዋች አምላክ እንደሚኖራቸው ሳይቀበሉ እንዳይቀሩ ተመኘሁ፡፡ ምንም እንኳን መፅሐፍ ቅዱስ ላይ በእኛ ይዘምራል፣ ይደንሳል ቢልም፡፡/ He will dance and sing over us/

ኢየሱስም በመቀጠል እንዲህ አለ . . . « ስለ እኔ ባህርይ ብዙ የተሳሳቱ መረዳቶች አሉ፡፡ ተጫዋችነት/Playfulness/ መካከለኛው የስሜ መጠሪያ ነው፡፡ ከሙሽራዬጋ መጫወት እወዳለሁ፡፡ ንፁህ የሆነ ሳቋንና አስደሳች የሆነውን ምላሿን

እወዳቸዋለሁ፡፡ ድንገት ላስደንቃትና ባርኔጣዋን በውኃ መውረጃ ውስጥ በመጣል 'ኦ! በመንግስተ ሰማያት ብዙ ጨዋታ አለ' ስትል መስማት  እወዳለሁ፡፡»

ጌታ በመንግስተ ሰማይ ሌሊት የለም ነገር ግን ይኸው በምሽት እየደነስን ነው፡፡

«በዚህ ምሽት አብረን እንድንሆን ለእኛ ያዘጋጀሁት የተለየ ሁኔታ ነው፡፡ ይህም አንድ ላይ እንድንሆንና አንቺ እጅግ ልዩ አድርገሽ በምትቆጥሪው ለምሳሌ እንደ ፕሮም ምሽት/ prom night/ ዓይነት ተደርጎ ነው የተዘጋጀው፡፡ ይህንን ያሰብኩት ቀደም ሲል በተገናኘንበት ጊዜ ነው፡፡»

« እምም. . . እንዴ ለምን? ከሆነ ነገር እየተመረቅሁ ነው እንዴ?»

«እንደዛ ነገር» አለኝ

‹እሺ»

«እየሄድሽ ነው ክሌር፣ ወደፊት እየሄድሽ ነው፡፡ አብረን ብዙ የምናከብረው ነገር አለን፡፡ ነገር ግን በመንግስተ ሰማያት ሆኜ ዝም ብዬ መጠበቅ  አልችልም፡፡ አሁን ከአንቺ ጋር ሆኜ መደሰት እፈልጋለሁ፡፡ እናም ለሙሽሮቼ እንዴት አፍቃሪና  እንዴት ጨዋታ እንደምወድ ንገሪያቸው፡፡ ስለዚህ ተዘጋጁ፡፡ »

## መልዕክት ሠላሳ
## የኔ ተፈጥሮ ማበረታታት ነው- ስለዚህም ምህረትን አድርጌያለሁ

{My nature is courage – I give to you My mercy}

"እዚህ ለሚቀሩት ግን እኔ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ እዚህ ሲቀሩ ለጥቂት ጊዜ በፍርሀት ሊሰቃዩ ይችላሉ፡፡ ቃሌ ይህ ነው በዓይን መግለጥ ፍጥነት ከእኔ ጋር በመንግስቴ ይሆናሉ፡፡ በሰማያት ያሉ ቅዱሳን በደስታና በጭብጨባ ይቀበሏቸዋል፡፡ ብዙ የሚሰዉ ሰዎች ስቃዩ አይሰማቸውም ምክንያቱም እኔ በመስቀሉ ላይ በራሴ ላይ አድርጌዋለሁ፡፡ አዎ እጅግ በጣም የሚያስፈራውንም ስቃይ እኔ ወስጄዋለሁ፡፡ ይህም ደካማ የሆኑትን ለመርዳት ነው፡፡ ምህረት የእኔ ተፈጥሮ ነው፡፡ ስለዚህም ለእያንዳንዱ የሚያስፈልገውን ድፍረት እሰጠዋለሁ፡፡ ሞትን ብቻቸውን አይጋፈጡም እኔ አብሬያቸው እሆናለሁ"

## ኢየሱስ የመንግስተ ሰማያትን ሚስጥር ሊገልጥ ቃል ገባ

{Jesus promises to revil the secret of heaven}

«ከእኔ ጋር እንድትኖሪ ወደ ቤቴ እወስድሻለሁ፡፡ እናም ወደ ሰማያዊው ገፀ-ምድር ይገቼሽ እሄዳለሁ፡፡ይህም ነገሮችን እንዴት በአንድነት ማስቀመጥ እንደቻልኩ የሚያሳየውን ሚስጥር ላስተምርሽ ነው፡፡ እነዚህም ነገሮች ከልጅነትሽ ጀምሮ ሲያስደንቁሽ ለነበሩ ነገሮች መልስ ለመስጠት ነው፡፡ በኮሜቶችና በከዋክብቶች መካከል ለመደነስ፣ ብርሃን በሚሰጡ ከዋክብቶች፣ ለእኔ በመዘመር ክብርን በሚሰጡ ከዋክብቶች ሥር ለመደነስ፡፡ እነዚህና ሌሎች ብዙ ለአንቺ ናቸው የኔ ዕርግብ፡፡ እጄን ይዞ ወደ ላይ መብረር ስንጀምር የቤቱ ጣራ ጠፋ፡፡ እናም ወደ ላይ፣ ወደ ሰማይ መብረር ጀመርን፡፡ በቅርቡ የተደባለቁ ቀለማት ያላቸውን፣ የተደራረቡ፣ ቀለማቸውን የሚቀያይሩ፣ እንዲሁም ፈዛዛ ቀለማት ያላቸውን በጠፈር ላይ ያሉ ብርሃናትን እናስሳለን፡፡ ወደ ላይ እየተንሳፈፍን ባለንበት ጊዜ ኢየሱስ ባለ ጅራታማ ኮከብ በእጁ ያዘና ለእኔ ሰጠኝ፡፡ ትንሽ ለስላሳ ኳስ የሚያህል ሲሆን ግን እንደ እሳት ዓይነት የሚያንፀባርቅ ነገር ይወጣዋል፡፡ ከእጄ ስለቀው የተለመደ መንገዱን ቀጠለ፡፡ በጣም የሚደንቅ ነው! ኮሜትን በመያዝ ጨዋታ!

## ህይወት በመንግስተ ሰማያት ምን እንደሚመስል - ስለ ሚሊኒየሙ መንግስት ትንሽ ፍንጭ

{What Life in Heaven is Like –Clues about the Millennium}

ጌታ ስለ መንግስተ ሰማያትና ስሚሊኒኒየሙ መንግስት እንዲህ በማለት መናገር ጀመረ . . . ይህ አሁን የማካፍላችሁ ርዕስ በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ እስካሁን ካወራነው ከባድ ርዕስ ይህ ትንሽ ዕረፍት የሚሰጥ ነው፡፡

## መልዕክት ሠላሳ አንድ
## በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ነገሮች እንዴት ነው የሚከናወኑት? እዛ ምን አለ?

### ኤፕሪል 26 ቀን 2015 ዓ.ም

{How do things work in Heaven? What is there?}

እንደምን አደራችው ውድ ቤተሰቦች ፣ ዛሬ ምሽት በጣም ቆንጆ የፀሎት ጊዜ ነበረኝ፡፡ ጌታ ይህንን ልምምዴን ለእናንተ እንዳካፍላችሁ ነግሮኛል፡፡ ዛሬ ምሽት ወደ አምልኮ ስገባ ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ጌታ ከጎኔ በቀኝ በኩል ተሰማኝ፡፡ ስለዚህ በልቦና አይኖቼ ስመለከት የሚወዛወዝ ወንበር ላይ ተቀምጠን አየሁ፡፡ ራሴን በትከሻው ላይ አስደገፌ እያለሁ በሙዚቃው መዝናናትና እርሱን ማምለክ ጀመርኩ፡፡ ያለንበት የአትክልት ቦታ ከሚያምሩ ቀለማት ያላቸው ህትመቶች ያሉበት መሆኑን ተመለከትኩ፡፡ ከዚህም በበለጠ መልክም መአዛ ያላቸው የአበባዎቹ ሽታ ያውድ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሽታው ኃይለኝነት የተነሳ ማሽተት አልቻልኩም ነበር፡፡ ለማንኛውም ከጥቂት ጊዜ አምልኮ በኋላ አንዳንድ የምወዳቸውን ክርስቲያኖች ፊትን ማየት ጀመርኩ፡፡ ኃዋሪያትን፣ ነቢያትን፣ የእምነት አባቶችንና የታመኑ የእግዚአብሔር ወንድና ሴት ልጆችን፡፡ ሁላችንም በአትክልት ቦታው ዙሪያ በደንብ እያመለክን ነበርን፡፡ የዩቱዩብ ቤተሰብ የሆኑትንና የተወደዱ ነፍሶችንም እዛ ለማየት እጅግ እጓጓ ነበር፡፡ እኔ እንደማየው እና እንደማሸተው የአትክልቱን ቦታ ቢያዩና ምክንያቱም እነሱም የጌታ ልብ ክፍል በመሆናቸው ነው፡፡ ጌታም እንዲህ አለኝ

«አንድ ቀን ይህ ራዕይ እነሱንም ያጠቃልላል፡፡ እናም ሁላችንም ባንድ ላይ እንደሰታን፡፡ ነገር ግን ለአሁን የእኔ ውድ ወንድና ሴት ሙሽራዎቼ ቤት ላዘጋጅላችው ሄጃለሁና ተፅናኑ፡፡»

« . . . ከንጥቀቱ በኋላ ስላለው መነጋገር እንቀጥል

«በመንግስተ ሰማያት ለእያንዳንዱ ውድ ሙሽራ መኖሪያን አዘጋጅቻለሁ፡፡ የእያንዳንዱን ምርጫ አውቃለሁ፡፡»

አዎ ጌታ አስተውያለሁ፡፡ (በነገራችን ላይ አባቴ የህንፃ ንድፍ አውጪ ስለሆነ በትንሹም ቢሆን ምርጫ ላይ ጠንቃቃ ነኝ፡፡ነገር ግን እርሱ የሚያምር ምርጫ አለው እና በጣም ጎበዝ ነው የሰው ልጅ ሊወደው የሚችል ምርጫ አለው፡፡ እንደ የእግዚአብሔር ዓይነት!)

ጌታም መናገር ቀጠለ . . . «አዎ እያንዳንዱ ቦታ ለእያንዳንዱ ሰው አመቺና ያማረ ነው ፡፡ የእያንዳንዳችሁን የቀለም፣ የቅርፅ፣ የምትወዱትን እንስሳ፣ የህንፃ አሰራር ፣ የምትወዱትን አበባና የተፈጥሮ አካባቢ አቀማመጥ ምርጫ አውቃለሁ፡፡ አንዳንዶቻችሁ የምትመርጡት የጋራ መኖሪያ ዓይነት ነው፡፡ እናም ለእናንተ ያዘጋጀውትን መኖሪያ ትወዱታላችው፡፡

«አንዳንዶቻችሁ ደግሞ በረሃ ትወዳላችሁ፡፡ ለእናንተም ያዘጋጀውት የቁልቋል ተክል፣ የምትወዷቸውን የተለያየ ቀለም ያላቸውን አበቦች፣ ከሰማይ ቀለም የበለጠ ሰማያዊ የሆነ የወራጅ ውኃ፣ አረንጎዴ ጥላና በውኃ ዳር የመደነሻ ሥፍራ እስከታዩ ድረስ ጠብቁ፡፡ ሁሉንም ትወዱታላችሁ፡፡

«አንዳንዶቻችው ደግሞ ባህር ዳርቻ ትወዳላችሁ፡፡ የምትወዱትን የቀንድ አውጣ ሽፋን፣ መጠን፣ ቀለም እና ማንጸባረቃቸው ሁሉ መርጬላችኋለሁ፡፡ ትላልቅ ዘንባባዎች እና ሰፋፊ ቅጠል ያላቸው የጫካ እፅዋት፣ ቴምር ና ትኩስ ኮኮናት ሁሉ አሉ፡፡ መቼም ቢሆን የማታክቱት መኖሪያ ይኖራችዋል፡፡

«ተራራማ ጫካ ለሚትወዱ ለእናንተ ደግሞ ስለዚህ ጉዳይ ክሌርን መጠየቅ አለባችሁ፡፡ ወይም መፅሐፏን አንብቡ በጣም ትደነቃላችሁ፡፡ ልብ ቅርፅ ያላቸው ሐይቅ፣ ለመዳሰስ የሚያሳሱ ቀላማት ያላቸው አሳዎች፣ ከባህር በታች ያለውን መስትዋት መሰለ ድንጋይና/Crystals/ ዋሻዎችን ሊያስጎበኙዋችው የሚችሉ ኤሊዎች፣ ከጎናችሁ እንዲራመዱ የምትፈልጉት የጫካ እንስሳት እንደ ድብ፣ አጋዘን ፣ የአጋዘን ግልገልና ሁሉም የምትወዱዋችው እንስሳት እናንተን እየጠበቋችሁ ነው፡፡ ብታምኑም ባታምኑም እነዚህ ሁሉ የእናንተን አብሮነት በትልቅ ናፍቆት እየተጠባበቁ ናቸው፡፡» እናም ከመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ሮሜ 8፡19-20 ሰጠኝ፡፡

<u>የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና።ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው።</u>

*ስለዚህ ፍጥረታት ሁሉ እንዴት እንደሆነ በማይታወቅ መልኩ በቅርቡ ሊሆን ስላለው ነገር እውቀት አላቸው፡፡ ልክ በመንግስተ ሰማያት ላይ በድንገት ሁሉ ነገር እንደ አዲስ ሲሆን ማለት ነው፡፡*

ጌታ መናገሩን እንዲህ በማለት ቀጠለ «ፍጥረታት ማን መሆናችሁንና ስማችሁን ሁሉ ያውቃሉ፡፡ ከእናንተ ጋርም በመግባባት ስሜቶቻቸውን ይጋራሉ፡፡ እንዲሁም በመንግስቱ ውስጥ ንፁህ ተድላ፣ ደስታና አንድነት ለመፍጠር ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህም ሁሉ ነገር በፍቅር የተሞላ ይሆናል ተብሎ እንደተፃፈ እንደዚያው በፍቅር የተሞላ ይሆናል፡፡

«ሙሹሮች ምን ያህል እየጠበኩዋችሁ እንደነበር ወደ ዘላለም መኖሪያችሁ ስትመጡ ይታወቃችዋል፡፡ በእርግጥም በጣም ከመገረማችሁ የተነሳ ለብዙ ቀናት ግራ ይገባችኋል፡፡ (ምንም እንኳን የሰዓት አቆጣጠር የተለየ መረዳት ቢሆንም)፡፡ ነገር ግን የፈጠርኩትን እያንዳንዱን ነገር በደንብ እያወቃችው ስትመጡ ትለምዱታላችው፡፡

"እንዲሁም ቢራቢሮዎች በምትወዱት ቀለማት፣ ወፎች ባስደናቂ ዜማቸው፣ ንቦች ሲዘምሩ እና ማራቸውን በለጋስነት ለማካፈል ሲፈልጉ፣ እንዲሁም በልብ ቅርፅ በመሆን ሲበሩና በእኔ ፍቅር መሞላታቸውን ለመናገር ሲፈልጉ ታያላችሁ ፡፡

«የሰው ልጅ ለክፋት ምልክት አድርጎ የተጠቀማችው እነዚያ ፍጥረቶች ሁሉ እኔ ምንም የማያውቁ አድርጌ እንደፈጠርኳቸው እንደ መጀመሪያው ፍጥረታቸው ይመለሳሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ በረዶው ጭልፊትና ጉጉት ዓይነት ከእናንተ ጋር በመስማማት የአካባቢው አባል ይሆናሉ፡፡»

«በመንግስተ ሰማያት ሞትና መሞት የለም፡፡ መወለድ ግን ይኖራል»

*ጌታ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?*

# መልዕክት ሠላሳ ሁለት
# በመንግስተ ሰማያት የመረዳት ስፋት ፤ደስታ፤የዕረፍት ጊዜና ተግባቦት

{Heaven: Dimensions of Awareness, Pleasure, Leasure and Communication}

«ወደ መንግስተ ሰማያት ስንመለስ፣ በመንግስተ ሰማያት ገና መለማመድ ያለባችሁ የመረዳትና የደስታ ልኬቶች ወይም ወርድና ስፋቶች/dimensions/ አሉ፡፡ አንዱን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ለማውጣት የጎበኘሁሽ ማታ አይተሸዋል፡፡»

*ኦ ጌታ! ያ ክስተት ለ45 ደቂቃ የተገለጠ ሰውነትንና ነፍስን የሚስደስትና ለመግለጥም የሚያዳግት ነው፡፡*

«አዎ በመንግስተ ሰማያትም አስደናቂነቱን ሁል ግዜ የማትረሱት እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ይከሰታል፡፡»

*ኦ እንዲህ ዓይነቱ ትኩረትን የሚስብ ነው፡፡*

«የሚሆነው ግን ሁልጊዜ በዛ ሁኔታ ላይ ሆናችሁ የነካችሁት ሁሉ ከዚህ ደስታ ተካፋይ እንዲሆኑ ነው፡፡ ምን ዓይነት ነገር እየጠበቃችው እንዳለ ምንም መገመት አትችሉም፡፡ በተለያየ ልኬቶች ወይም ወርድና ስፋት/ inter-dimensionally/ የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ በአንድነት በመሆን እንዴት እርስ በርሳችን በፍቅር እንደምንግባባ ታያላችሁ፡፡»

"ምን ማለት ነው?

«እሺ ይህ ማለት ዕፅዋት በአንድ ልኬት ወይም ወርድና ስፋት /one dimension/ ይግባባሉ፣ ድመቶች በሌላ ልኬት፤ እንዲሁም ድንጋዮች በሌላ ልኬት ይግባባሉ፡፡ ነገር ግን ፍጥረትን ሁሉ በአንድ ላይ የያዘው ፍቅር ደግሞ ልዩ ልዩ ፍጥረታትን እርስ በርስ አስተሳስሯል፡፡ በሌላ አባባል ፍጥረታትን ሁሉ ታናግራላችሁ እነርሱም ገብቷቸው ይመልሳሉ፡፡ እናንተም እነርሱ የሚሉት ይገባችኋል፡፡ በስተመጨረሻም ይህ ሁሉ ለእኔ ክብርን ያመጣል፡፡»

*ኃያሉ እግዚአብሔር ምስጋናና ክብር ሁሉ ለአንተ ይሁን!*

«አዎ ሁላችንም በአንድት በማያቋርጥ የተድላና የደስታ አምልኮ ውስጥ እንሆናለን፡፡ ሁሉም ፍጥረቶቼ በሚያስደንቅ የደስታና የተድላ ምስጋና ከእኔ ጋር አንድ ይሆናሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ምንም ነገር ተለማምዳችው አታውቁም፡፡»

# መልዕክት ሠላሳ ሦስት
# የመለየት ችግርና የመንግስተ ሰማያት ጨረፍታዎች

**ሜይ 8 ቀን 2015 ዓ.ም**

{Troubling discernment & glimpses of heaven}

*መንግስተ ሰማያት፡- ከማስደነቅ የሚያልፍ ሥፍራ ነው፡-*

*እየተራመድንበት የነበረው ሰርጥ በጣም ረጅም፣ ጨለማና የእሳተ ጎመራ የቀለጠ ድንጋይ ያለበት ገደል ነበር፡፡ ንፋሱ በኃይል እየመጣ ነበር፡፡ ነገር ግን ወዲያው ወደ ውኃው ስንቀርብ ማዕበሉ በጣም በተረጋጋ ዓይነት ወደታችና ወደላይ በቀስታ መዝለል ጀመረ፡፡ ይህም እኛን ሰላም ለማለትና ጉዟችንን በፀጥታ ሁኔታ እንድንራመድ የሚደርግ ዓይነት ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ የሆነው ነፋሱ ፊቴ ላይ ሮዝ ቀለም ያለው ፊርጥ ከረጨብኝ በኋላ ነበር፡፡*

*ጌታ እየሳቀ ተመለከተኝ፡፡ «አንሽው» አለን፡፡ ፊርጦቹን ማንሳት ስጀምር ከውስጡ ብዙ እንቁዎች፣ የሚያስደነቅ ቀለማት ያላቸው የከበሩ ድንጋዬች መውጣት ጀመሩ፡፡ በእጇ ሰበሰብኳቸውና በአየር ላይ በተንኳቸሁ፡፡ ይህንን ካደረኩ በኋላ ግን ማስቀመጥና ሌሎችን ማካፈል ነበረብኝ ብዬ ለራሴ አሰብኩ፡፡ ልክ ይህንን እንዳሰብኩ ከፊርጡ የወጡትና በአየሩ ላይ የበተንኳቸው የከበሩ ድጋዬች ሁሉ ከአፈሩ ላይ እየተነሱ ወደ ፊርጡ መመለስ ጀመሩ፡፡*

*ወዲያውም እንደ ብርችቆ ጥርት ያለ ወንዝ ዳር ተቀመጥን፡፡ ይህም ወንዝ የሚፈሰው ወደ ባህር ነው፡፡ አረንጎዴ ላባዎች በመስመር ድንጋዮቹን በመሸፈን በውኃው ስር ተኙተው ነበር፡፡ ምን እየበላን እንደነበር አላስታውስም፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ እንዲህ አለኝ … «አ ችግር ተፈጠረ»፡፡ ከዛም ጁድሃ የሚባለው የአፍሪካ ወንድ አንበሳ መጣ፡፡ ጁድሃ ወደ ወንዙ ዳርቻ ልክ በምሳ ሰአት የመጣው በሞገስ ነበር፡፡ ከያዝነው ምግብ ትንሽ ሰተነውና በትንሹ ፈገግ አልን፡፡ ከጀርባዬ ስመለከት በትልቅ ሳህን ሥጋ የሚመስል ምግብ ብቅ አለ፡፡ ይህም የጁድሃን ትኩረት ሁሉ ሳበና እኛን ረስቶ በራሱ አለም ቀጠለ፡፡*

*ወዲያውም ግሪሲ የምትባለው የምታምር ድመታችን የራሷን ድርሻ ለመጠየቅ እየጮኸች ተቀላቀለችን፡፡ እንደገናም ሌላ ድመታችን፣ እንዲሁም ትንሹ ጁድሃ አንበሳ ተቀላቀሉን፡፡ እንደገናም የተራራው አንበሳ አይነት ምልክት ያለባት አቢሲኒያን ድመት ወደ እኛ መጡ፡፡ ጁዳህ በተፈጥሮው በጣም ያሸታል፡፡ እናም ከመቀላቀሉና እናንተን ከመቀበሉ በፊት የተለያዩ ቦታዎችን ወደ ዘጠኝ ጊዜ ሊያሸት ይችላል፡፡ ትልቁ ጁድሃ ከማስፈራት ውጪ ረጋ ባለ መልኩ ጎሸም አድርጎ ሰላምታ ሰጠው፡፡*

*ምሳችንን በልተን እንደጨረስን እግሬን ውኃ ውስጥ ለመንከር ተነሳሁ፡፡ በዚህ ጊዜ የሆኑ ሰዎች ወደ ወንዙ ዳር እየሮጡ መምጣት ጀመሩ፡፡ ኦ በጣም በደስታ በዙሪያችን ተሰባሰቡ፡፡ የሚመስለው ለብዙ ጊዜ ተጠፋፍተን የተገናኘን ጓደኞች ነበር፡፡ ልብሴን ፀጉሬን በመዳሳትና በፍቅር መነካካት ጀመሩ፡፡ ኢየሱስ በወንዙ ዳር ተቀምጦ እያለ በጀልባ ወደ ሸለቋማ ቦታ ሊወስዱኝ እንደፈለጉ ነገሩኝ፡፡ ወዲያው ጓደኞች በመሆን እየተደሰትን በረጋው ወንዝ ላይ አብረን እየተንሳፈፍን መጓዝ ጀመርን፡፡*

*ይህ ጉዞዬ አጭር ነበር፡፡ ኢየሱስ በጣም ቀንቶ ስለነበር ሙሽራውን ሊታደግ በውኃው ላይ እየተራመደ መጣ፡፡ ሌላ ራቅ ወዳለ ሥፍራ ወሰደኝ፡፡ ይህም ሥፍራ እንደ ብርጭቆ ጥርት ያለና የረጋ ውኃ ያለበት ቦታ ነው፡፡ በመሬት ላይ ቆሜ*

ውኃውን ውስጡን ስመለከት በትንግርት ቀለማት ያሸበረቁ አሳዎች ነጭ አሸዋ የተጠነፈ በሚመስል ላይ ሆነው ተመለከትኩ፡፡ የአሳዎቹ ቀለም የቀስተ ደመናን ቀለማት ሁሉ የያዘና እጅግ የሚደንቅና የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

ጌታና እኔ ወዲያው ከአሳዎቹ ጋር መዋኘት ጀመርን፡፡ እናም ከውኃ በታች የሚገኘውን የሚደንቅ ምድር እያዞረ ያሳየኝ ጀመረ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ቦታ ያየሁት ሜክሲኮ በሚገኝ ዩካታን በሚባል ውስጥ እንደሆነ አስታውሳለሁ፡፡ ያ ሥፍራ ቱሪስቶች የሚጎበኙት ሥፍራ ነው፡፡ በዛ ያሉ አሳዎቹም የሚያዙ ዓይነት ናቸው፡፡ እንደዛ ዓይነት አይቼ አላውቅም፡፡ ሥፍራው የሚመስለው ከውኃ በታች የሚገኝ እጅግ ድንቅ ቀለማትን ሁሉ ያሰባሰበ ነገር ግን ደግሞ የብርጭቆ ውኃ ውስጥ ያሉ መስሎ ነው የሚታያችሁ፡፡

«የተወደዳችሁ በዚህ ምድር ስትኖሩ ጠባሳ፣ ቁስል፣ ስብራት፣ ባዶ ቦታዎች ያሉባችሁና በእርግጥም በጦርነት የቆሰላችሁ ናችሁ፡፡ በመንግስተ ሰማያት ግን ሁላችሁም ትታደሳላችሁ፡፡ የፈጠራ ችሎታችሁ እጃችሁ በነካው ነገር ሁሉ ይታያል፡፡ በምድር ላይ ተሸፍኖ የነበረው የእናንተ ክፍል በመንግስተ ሰማያት ውስጥ በሙላት በማበብ ሽታው የመንግስተ ሰማያት ምክር ቤት ያውዳል፡፡ በእርግጥም በፍጥረት ጊዜ የእግዚአብሔር መልክ እንድትመስሉ አድርጎ የፈጠራችሁ ማንነታችሁ አብቦ እጅግ ግሩም የሆነ ሽታ ያለውን አበባ እንዲሁም እጅግ ጣፋጭ የሆነውን ፍሬ ያፈራል፡፡ በእናንተ ውስጥ የተቀመጠው ቅባት ለመጀመሪያ ጊዜ በነፃነት መፍሰስ ስለሚጀምር ስጦታዎቻችሁ ሌሎችን መፈወስ ይጀምራል፡፡ በነፃነት እንዲሁ መፍሰስ ይጀምራል፡፡ ሩቅ ባለው መንግስተ ሰማያት ክፍል እንኳን በመድረስ የነካችሁት ሁሉ እንዲፈወስ ያደርጋል፡፡

«ከዚህ የሚበልጥ ሊያስደንቅ የሚችል ነገር አለ? እኔ ለእናንተ እንዲህ እላለሁ "አይኖርም"፡፡ መንግስተ ሰማያት ከማስደነቅም ያልፋል፡፡ መንግስተ ሰማያት በምድር ላይ በአጭር የህይወት ዘመናችሁ የተመኛችሁትን ሁሉ የምታገኙበት ቦታ ነው፡፡

«በዚህ ምድር በህይወት ስትኖሩ ‹እንደዚህና እንደዚያ ቢሆን› እያላችው ታስባላችሁ፡፡ ለመሆኑ ታውቃላችሁ መልአካችሁ ይህንን ሁሉ እየመዘገበ ለእኔ እያመጣ እንደሆነ? አ! አዎ መልዕክቶቻችሁ በዚህ ችሎታም ያገለግላሉ፡፡ ለእናንተ ደስታን ሲያመጡ ማየት ለእኔ ደስታ ይሰጠኛል፡፡ መላዕክቶችም የሚኖሩት ለሌሎች ደስታን ለማምጣት ነው፡፡ ይህ ራሱ ለእነርሱ ደስታን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህም ለእናንተ ከፈጠርኩት አንዱን ድንቅ ቦታ ስትጎበኙ ለዘመናት ስታስቡት የነበራችሁትን እያንዳንዱን ነገር የሚያጠቃልል ነው፡፡»

«ለምሳሌ አንድ ወይን ጠጅ ቢራቢሮ አይታችው ውይ ክንፏ ላይ አይን ቢኖራት ብላችው አስባችው ከነበር ያ ኃሳባችሁ ተቀድቷል፡፡ እናም በመንግስ ሰማያት ያንን ቢራቢሮ ስታዩ ክንፋቸው ላይ ዓይን ይኖራቸዋል፡፡› እንዲሁም ቀይ ድንጋይ ብትወዱ፣ እንዲሁም ወራጅ ውኃ ያለበት ጥልቅ የሆነ ሸለቆና የምትወዱት ዕፅዋት ቢኖር ልክ እደዚያው እንደምትወዷቸው ታገኙታላችሁ፡፡ በሁሉም አቅጣጫ እናንተ እንዲህ ቢሆን ብላችሁ ያሰባችሁት ሁሉ እንደዛው እንዳሰባችሁት ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ »

«ሁሉ ነገር እንዴት በፍቅር እንደተሞላ ለውጡን ታያላችው፡፡ አንበሳና ግልገል አንድ ላይ ጎን ለጎን ተጋድመው፣ እናም ሲያንቀላፉ አንበሳው ግልግሉን አቅፎት ታያላችሁ፡፡ በውኃ ውስጥ የሚኖረው እንስሳ በውኃ ውስጥ እየዋኘ እያለ በጣም የሚያምር ሼል በእግራችሁ ሥር ይጥለዋል፣ እንዲሁም ንቦች በልብ ቅርፅ እየበረሩ ማራቸውን እንድትበሉ ይጋብዟችኋል፡፡

‹‹አሸዋው ለናንተ ምቾት ለመስጠጥ በቅርፅ ራሱን እያስተካከለ እናንተ እንዲመቻችሁ ያደርጋል፡፡ የሸለቆዎች ግርግዳ ያለምንም ልፋት ለመውጣት እንድትችሉ የእግር ማስቀመጫና እጅ መያዣ ይኖራቸዋል፡፡ ከሸለቆው ስትወጡ በመንገዳችሁ ትንንሽ አስደናቂ ዋሻ የሚመስሉ ነገሮች ጥርት ባለ በተለያዩ ዓይነት ፈርጦች ታገኛላችው፡፡ ንስር አሞሮች በጎጆዋቸው ውስጥ እንድትቀመጡና ህፃናቶቻቸውን እንድትካከሉላቸው ይጋብዟችኋል፡፡ የዛፍ ቅጠሎች በአጠገባችሁ ስታልፉ በደስታ ያኮሻኩሻሉ፡፡ ሳሮችም ልክ ቃጭል እንደሚያቃጭል እናንተን ሰላም ለማለት ያቃጭላሉ፡፡ ኦ! በመንግስ ሰማያት ያሉ አስደናቂ ነገሮች አያልቁም፡፡ እነዚህ ሁሉ የእናንተ ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም በምድር ላይ የኖራችሁት ለእኔ ነው፡፡ ስለዚህም አሁን ደግሞ ዘላለማዊ ህይወትን ባልጠበቃችሁትና ባላሰባችሁት ዓይነት ደስታ እሞላችኋለሁ፡፡ ይህም በምድር ሆናችሁ የመሰጣችሁ ህይወት ነው፡፡ በሚያስደስት ሁኔታ አብረን እንኖራለን፡፡

‹‹ለሙሽሮቼ የመንግስተ ሰማያት አንዳንድ አስደናቂ ነገሮችን ለማካፈል እፈልጋለሁ፡፡ እንደገናም ደግሞ በግሪክ ውስጥ ያለውን ብዙዎች የሚያደንቁትን የጥንት ቦታዎች ዓይነትም እንደሚኖር ልነግራቸው እፈልጋለሁ፡፡ እንዲሁም ቡና መጠጫ ቤቶችና /Café/ የስዕል ሥራዎች በትንንሽ ምግብ ቤቶች ግድግዳዎች ላይ ተጣብቀው ይገኛሉ ፡፡ በጋራ መኖሪያ ቤት /apartments/  መኖር ለሚወዱ ራሳቸው በሚወዱት ዓይነት አሰራር መሰረት መኖሪያ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ከፊት ለፊት ለማየት  በሚያምር በረንዳና ለዕይታ በሚማርክ የመሬት አቀማመጥ፣ እንዲሁም አበባዎችና የውኃ ፋውንቴን እያዩ እንዲኖሩ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በረንዳቸው ላይ ተሰብስበው እርስ በርስ መጫወት ወይም አንዱ ሌላውን መጎብኘት ይችላሉ፡፡ ጥዝምዝ ያሉ አበቦች በአትክልት ቦታዎቻቸው ፣ጥንታዊ ድልድይና ሰፊ የኮብል ድንጋይ መንገድ፣ ሊሊ አበባ ያሉባቸው ስወር ያሉ የአትክልት ቦታዎች፣ እንዲሁም የውኃ ጅረት እና ምቹ የሆነ የሚወዛወዝ መቀመጫ የሚገኙበት ነው፡፡ ኦ! በከተማ መኖር ለሚወዱት ያዘጋጀሁት ከዚህ አለም በፍፁም ይለያል፡፡››

ጌታ አንተ ምንም ግማሽ ነገር አትሰራም፡፡ አንተ በጣም አፍቃሪ ነህ ማንም እንዳንተ ሊያፈቅረን የሚችል የለም፡፡

‹‹ሙሽራዬ ይህንን ያህል እንኳን ለመንግስት ሰማያት ጉጉት የላትም፡፡ የሄድኩት ለእርሷ መኖሪያ ለማዘጋጀትና የማያቋርጥ ደስታ ለማምጣት እንደሆነ ትንሽም የገባት ነገር የለም፡፡ ለእርሷ የማያልቅ ደስታ ብቻ ለማምጣት፡፡ ስለዚህ ሙሽሮቼ ሁሉ ይህንን እንድታስታውሱ እፈልጋለሁ፡፡  የሄድኩት ሥፍራን ላዘጋጅላችሁ ነው፡፡ በእርግጥ ለእናንተ ሥፍራን ላዘጋጅላችሁ ነው፡፡ እኔ ባለሁበት እናንተም በዛ እንድትሆኑ ነው፡፡ እናም ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ የሚዘጋጅላችሁ ዝም ብሎ እንደማንኛውም ስፍራ አይደለም፡፡ ቦታው እጅግ አስደናቂ ምድር/ wonderland/ እንዲሁም ለእናንተ ሲባል የተዘጋጀ የጥበብ ሥራ  ያለበት ነው፡፡

‹‹ይህንን ዕይታ አሁን ውሰዱ፡፡ እናም  በቅርብ ስለምመጣ ልባችሁን አዘጋጁ፡፡ ይህንን በልባችውም አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ በልባችሁ ትልቅ ቃብት አድርጋችሁ አስቀምጡት፡፡ በልባችሁ ውስጥ ትዝ ሲላችሁ ደስታን ይሰጣችኋል፡፡ ምክንያቱም የእኔ ልብ በእናንተ ውስጥ ደስታንና መደነቅን ለነፍሳችው ይሰጣል፡፡

"‹‹አሁን በፍቅሬና በቅርቡ ለዘላለም አንድ ላይ እንሆናለን ብዬ በገባሁላችሁ ቃል እባርካችኋለሁ፡፡››

## መልዕክት ሠላሳ አራት
## በመንግስተ ሰማያት የሚሆነው እንዲህ ነው፡
## ከክርስቶስ ጋር የሚኖራችሁ ግንኙነት

{This is how it will be in heaven: your relationship with Jesus}

ጌታ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . «ኦ ወንድና ሴት ልጆቼ እኔ ወደ እናንተ የመጣሁት እንደ ፍቅረኛ ነው ፡፡ ምክንያቱም ከህይወታችሁ ሙሉ ክፍል እንዴት መተሳሰር እንደምፈልግ ልታውቁ የምትችሉት በዛ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ሴቷን ለአዳም የምትመች አድርጌ ስፈጥርለት ለማሳየት የፈለግሁት እኔ ከእናንተ ጋር እንዲኖረኝ የምፈልገውን ህብረት ነው፡፡ በእናንተ ላይ ያቀድኩትን የህይወት ዘመን መሰጠት ማስፈለጉን ለይቼ ሳላሳያችሁ ለመባዛት የሚያስችላችሁን ኃይል ብቻ ልሰጣችሁ እችል ነበር፡፡ እናም በዚህ መልኩ ቢሆን ኖሮ የእንስሳት ዓይነት ህይወት ይኖራችሁ ነበር፡፡ በአንፃሩ ግን እኔ ለማሳየት የመረጥኩት ከእናንተ ጋር ለዘላለም ህብረት ለማድረግ ፍላጎት እንዳለኝ ነው፡፡ በህይወት ስትኖሩ የሚገትማችሁን ደስታና ኃዘን ለመካፈልና ከዚህም ሁሉ ባለፈ ከተፈጠረው ነገር በበለጠ ወደእኔ መጥታችሁ በእኔ ላይ ትጣበቃላችሁ በሚል ተስፋ ነበር፡፡ በዚህም አብረን መንፈሳዊ ልጆችን እናፈራለን በሚል እሳቤ ነበር፡፡

« ከእኔ ጋር ያላችሁን ግንኙነት አትፍሩ እያልኩ የምጠይቃችሁ አንዱም ምክንያት ይህ ነው፡፡ ይህ ተፈጥሯዊና እኔ በእናንተ ህይወት ውስጥ ማን መሆኔን በሙሉ መልኩ መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

«በምድር ላይ ከእኔ ጋር ባላችሁ ህብረት መጠን ነው በመንግስተ ሰማያት ውስጥም የሚሆነው፡፡ በምድር ስትኖሩ ሁሉን በሙተው ሁሉ ነገራችሁ እኔ ከሆንኩ፣ በመንግስተ ሰማያትም ልትይዙ በምትችሉት መጠን በሙላት ታገኙኛላችሁ፡፡ ነገር ግን በምድራዊ ነገር ተመስጣችሁ አለምን ከእኔ ይልቅ ከመረጣችሁ በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ጥሩ ሥፍራ ታገኛላችሁ፡፡ ነገር ግን ከምርጫችሁ የተነሳ የክብር ደረጃችሁ የተገደበ ይሆናል፡፡

«የሰው ልጆች የማሰብ ችሎታ ወርድና ስፋት/Dimension/ በላይ ካልሆነ በቀር ማንም ይህንን ሊረዳ የሚችል የለም፡፡ ይህንን ፀጋ ነው እግዚአብሔር የሰጣችው፡፡ ወደ እኔ በተጠጋችሁ መጠን አይምሯችሁ እኔን መረዳት እንዲኖረው አደርጋለሁ፡፡ ከእኔ ጋር ያላችሁን ግንኙነት እየኮተኮታችሁ በሄዳችሁ ቁጥር የኔ እየሆናችሁ ትሄዳላችሁ፣ እኔም የእናንተ እየሆንኩ እሄዳለሁ፡፡ ከሌሎችም ጋር በሆናችሁ ጊዜ የኔ መገኘት አይጠፋባችሁም፡፡ ምክንያቱም እኔ መጠን የሌለኝና የማልገደብ ነኝ፡፡ ስለዚህ ሌሎችም አብረዋችሁ እያሉ የኔን የመገኘት ሙላት ትለማመዳላችሁ፡፡ ይህ ምስጢር ነው፡፡ ይህንን እንዳለ ተቀበሉትና የእናንተ ሁለመና መሆን እንደምፈልግ እወቁ፡፡ በምላሹም እኔ የሆንኩትን ሁሉ እሰጣችኋለሁ፡፡ እናም እናንተ የታወቃችሁትን ያህል እንኳን እኔን ማወቅ ይሆንላችኋል፡፡

«ማለቂያ የሌለው ጥያቄዎቻችሁን አቁማችሁ ወደ እቅፌ እንድትገቡ እየጠበኩዋችሁ ነው፡፡ ኑ እኔ እንደ ውቅያኖስ የሰፋና የማያልቅ ሰላም አለኝ፡፡ በዚህ በማያልቀው ሰላሜ ውስጥ ግቡና ለነፍሳችሁ ሰላምን ታገኛላችሁ፡፡»

# መልዕክት ሠላሳ አምስት
# ለነፍሳችሁ ዕረፍት አግኙ

{Rest for your soul}

"ፈጣሪህን ከፈጠረው ነገሮች ሁሉ አስበልጠህ ምረጠው"

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . ይህንንም ምርጫ ማድረግ እንድትችሉ ነፃ ምርጫ ሰጥቼአችዋለሁ ። ስለዚህም አለምን ሁሉ ዞራችሁ፣ አይታችሁና መርምራችሁ በመጨረሻ ተስፋ የማደርገው ምርጫችሁ ወደ ቤታችሁ በመመለስ በልቤ ውስጥ ለዘላለም ትኖራላችሁ ብዬ ነው። አ! የኔ ድንቅ ፍጥረቶች የፈለጉትን እንዲመርጡ ፈቃድ ሰጥቼያቸው እያለሁ እነርሱ ግን እኔን ብቻ በመምረጥ ወደ እኔ ተመልሳ ትመጣለች ብዬ እንዴት እየጓጓሁ እንዳለሁ (የክርስቶስ ሙሽሪትን ሁሉ ይመለከታል)!። ወደ እኔ ተመልሳ ስትመጣም በአንድነት እንደሰታለን። ይህም ደስታ መላዕክቶች እንኳን ለዝማሬ የሚያነሳሳ ዓይነት ደስታ ነው። የህይወትሽ ወሳኙ ቀን ፈጣሪሽ ከፈጠረው ነገር ሁሉ እርሱን የመረጥሽበት ቀን ነው። ስለዚህ የህይወትሽ ፍፃሜ ሙሉ በመሆን ወደ እኔ ተመልሰሽ ለዘላለም እኔን ማምለክና ማክበር ይሆናል። እናም አይኖቼ አንቺን ከማየት፣ ጆሮቼም አንቺን ከመስማት፣ እጆቼም አንቺን ከመያዝ አይታክቱም።

"ለመሆኑ ምን ያህሉ ወጥተው ሳይመለሱ በዛው ቀልጠው እንደሚቀሩ ታውቃላችሁ ? እነዚህ በአንድ ጨለማ ጥግ ተጣብቀው ቀስ በቀስ እየራቁ ይሄዳሉ። ሊኖሩበት የተሰጣቸውን ብርሃንና ደስታ ብሎም ህይወት ቀስ በቀስ በማጣት ጨለማ ይውጣቸዋል። አህ! ምን ያህል አሳዛኝ ነገር ነው! እጅግ የተወደደው የህይወት ክፍል ትርጉም አልባና መሰረተ ቢስ ሆኗል። ታዲያ የእነዚህ ወደ እኔ መመለስ የበለጠ ውድ እና የተፈቀሩ ያደርጋቸዋል። አ! ከዚህ ውጤቱ እጅግ አሰቃቂ ከሆነ ነገር በህይወት ለመኖር መጀመር እጅግ ውድ ነገር ነው።

"አያችሁ ይህ የተካፈላችሁት መለኮታዊ ባህሪ እጅግ አስደናቂ፣ ልዩና ግላዊም ነው። ይህንንም ሙሉ በሆነ መልኩ መገንዘብ የምችለው እኔ ብቻ ነኝ። ማድነቅም የምችላው እኔው ብቻ ነኝ። ደግሞም ልፈፅመው የምችለው እነው ብቻ ነኝ። ለመፈፀምና ለማሳካትም ቁልፉ ያለው እኔውጋ ብቻ ነው። ይህ ብቻውን የላቀ ሚስጥር ያለውና ትልቅ የደስታ ውቃያኖስን የሚፈጥር ነው። "አዎ፣ የእኔ ፍቅሬ፣ የኔ ትንሿ፣ የደስታ ውቅያኖሶችን ፍጠሪ፣ በዘላለማዊ የአምልኮና የምስጋና እንቅስቃሴ ውስጥ ግቢ። በህይወት በመገኘትሽና በአምላክሽ ህይወትን በመጎናፀፍሽ ማድረግ የምትችይው እኔን በማምለክ ደስታሽን መልሰሽ ለእኔ ማቅረብ ነው። እኔ ደግሞ የማደርገው የኔ ግማሽ አካል፤ የስጋዬ ቁራጭ፣ የአጥንቴ ፍላጭ የሆነችው ከሁሉ እኔን መርጣ ወደ አባቷ በመመለስ ለተሰጣት ማንነት የህይወትን ዳንስና ምስጋና ስታቀርብ በደስታ ምክንያት ዓይኔ በዕንባ ተሞልቶ ጥልቅ ፍቅርሽን ማድነቅ ነው።

"አህ፣ ይህ እጅግ ታላቅ ምስጢር ነው። ማንም ሊገባው የማይችልና እኔ ብቻ እውነቱን ተገንዝቤ ላደንቀው የምችለው ጉዳይ ነው። በድካም ውስጥ ሆናችሁ ዓይናችሁን ጨፍናችሁ እንኳን እያለ በደስታ ውስጥ እንጨፍራለን። ይህም ዘላለማዊ ህይወት የተመሰረተው በፈቃድ በመመለስ ውስጥ ነው። ይህም መመለስ ወደ ትውልድ ሥፍራዋ፣ ብቸኛ ደስታና እርካታ ወደሚሰጣት ሥፍራ የሚያመጣት ነው። ይህ እንዲሆን እኔ ብዙ ጊዜ ጠበቅሁ፣ ጠበቅሁ፣ ጠበቅሁ። እናም በመጨረሻው አንድ የትውልድ ቦታዋን በመፈለግ የመንግስተ ሰማይን መስከ አቋርጣ እየቧረቀች መጣች።

"ኦህ, ክሌር! የራሴ ሥጋ እና አጥንት ሲመለስ የተሰማኝን ደስታ ለመግለፅ ምንም ቃላት የለኝም፡፡ ይህ ከቤተሰቡ ታላቅ ምስጢር አንዱ ክፍል ነው፡፡ ይህ ትልቁን የህይወት ክፍል የሚያሳይ እጅግ ትንሹ ክፍል ነው፡፡ አባት የሆንኩት እኔ የህይወት ፍሬ የሆነውን ነፃነት ለዘላለም ከእኔ ጋር እንድትመርጪ ወይም እንድታጥላይው ነፃነትን የሰጠሁሽ በዚህ አለሁ፡፡ ይህም በነፃነት የውሸትን ህይወት ወይም የእውነትን ህይወት እንድትመርጪ የሚያደርግ ነው፡፡ ኦ! የሰው ልጅ ሊገባው የሚገባ ነገር ግን ገና ያልገባው እንዴት ድንቅና የላቀ ነገር አለ፡፡ እናም በመንግስተ ሰማያት ይህ እውን ይሆናል፡፡ እናም አርቆ ማስተዋል ይሆንላችኋል፡፡ አርቆ ማስተዋል የሚያስፈልገው ይህንን ትልቅ የፍጥረት ሚስጥር ለመረዳት ነው፡፡ እናም እያንዳንዱ ወንድ በአንድ ሴት ፍፃሜ እንዲያገኝ ለምን እንዳቀድኩና ሁለቱ በአንድ ላይ ዘር እንዲያፈሩ እንዳደረኩ ያን ጊዜ ይገባችኋል፡፡

"ይህ የነገርኳችሁ በጥቂቱ እንድትረዱ የሚያደርግ ትንሽ ዘር ነው፡፡ ውጤቱ በትልቅ ክብር እንዲያልቅ ካቀድኩት የህይወት ውደት (life cylce) በጣም ለጥቂት ጊዜ የሚቆየውን ነው፡፡ አሁን የምፈልገው እነዚህን የህይወት መሰረታዊ ነገሮች እንዲሁም የእናንተ ነገር ለዘላለም በእጄ ላይ ሊፈፀም የቀረው ጥቂት ጊዜ እንደሆነ አውቃችሁ ደስ እንድትሰኙና በጥልቅ እንድታሰላስሉት ነው፡፡

" አሁን እያንዳንዳችሁን በማያልቀው ፍቅሬ እባርካችኋለሁ፡፡ በቅርቡ ወደ መጨረሻው የመኖሪያ ሥፍራችሁ ስለምትደርሱ እባካችሁ አለምን በሙተው ቀጥሉ፡፡"

# መልዕክት ሠላሳ ስድስት
# ኢየሱስ የመታዘዝ ዋጋ ምን እንደሆነ ይናገራል

**ሜይ 17 ቀን 2015 ዓ.ም**

{Jesus speaks the high value of obedience}

*ኢየሱስን እንዲህ ብዬ ጠየኩት . . . በዚህ ምሽት ውድ ለሆነችው ሙሽራህ መልዕክት አለህ?*

ኢየሱስም እንዲህ አለኝ . . . «በርግጥ አለኝ፡፡ ከምገልፀው በላይ ቆንጆ ናት፡፡ እያንዳንዱ እርምጃዋና እያንዳንዱ ምልከታዋ በቅድስና ተባርኳል፡፡ ምክንያቱም የእኔ ናት፡፡ መቶ በመቶ ራሷን ለእኔ ሰጥታለች፡፡ መታዘዟ ውበት ብቻ ሳይሆን አስደናቂም ነው፡፡ የቀረው ዓለም ሁሉ ለራሱ ፍላጎት ወዲህና ወዲያ ሲሯሯጥ የእርሷ እግሮች ግን በመታዘዝ ወደ አምላኳ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ በምትወስደው እርምጃ የእግሮቿን ውበት አታያቸውም፡፡ ነገር ግን ይህ ብቻ እንኳን እሷ በምታልፍ ጊዜ የመለኮት ሽታን ከኋላዋ ጥሎ ያልፋል፡፡

"የመታዘዟን ዋጋ በስዕል ባስቀምጠው የምታዩት ወርቃማ ጫማ የተጫማ በጣም የሚያምሩ ፍፁም የሆኑ፣ በእንቁና በጌጣጌጥ ያሸበረቁ እግሮችን ነበር፡፡ እያንዳንዱ እርምጃዋቿ የሚያስደንቁ ዜማን የሚያወጡ ናቸው፡፡ እግሮቿን ለመራመድ ባነሳሳቸው ጊዜ የባህር አበቦች ወዲያው ተነስተው መዓዛቸውን ይሰጣሉ፡፡ ብርሃናትም ተሰብስበው ብርሃናቸውን ይሰጣሉ፡፡

«የተሰጣት ሥራ በከበደ ቁጥር የሚያስደንቅ ድምፅ ታወጣለች፡፡ አበቦችና ፍሬዎች የበለጠ ያፈራሉ፡፡ በየቀኑ በአረጀ መንገዶች ላይ ስትራመድ በዳርና በዳር ያሉ የአትክልት ዛፎች በማበብ መዓዛቸው ማወድ ይጀምራል፡፡ የመጨረሻ ያረጁና በጦርነት የተጎዱ ነፍሶች እንኳን ቀስ በቀስ ዘላቂ የሆነ ጣፋጭ ፍሬ ያፈራሉ፡፡»

«ለእኔ የመታዘዟ ትርጉም ይህ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቶቹ የፍቅር አበቦች ምድር እንዳሉት አበቦች መቼም አይጠወልጉም፡፡ በፍፁም፣ እንዳውም እንደነሱ ዓይነቶቹን በመጨመር ጫካ እስኪሆን ድረስ ይበዛሉ፡፡ ደግሞም እነዚህ አበቦች የሚቀጠፉና ከመልካም መአዛቸው ጋር ለዘላለም የሚቆዩ ናቸው፡፡ እንደገናም ወደ አትክልት ስፍራዋ በመሄድ ዛፎቿና አበባዎቿ አብዝተው እንዲያፈሩ እገርዛቸዋለሁ፡፡ ይህ የአትክልት ሥፍራ እንዴት የሚያምርና የተዘረፈሩ ቅርንጫፎች በጥንቃቄ መደገፊያ ተደርጎላቸው ለመብላት እንደሚያስጎመጁ ሁሉ ለዓይንም እጅግ ማራኪ ናቸው፡፡

"አያችሁ መታዘዝ ትንሽ ነገር አይደለም፡፡ ደግሞ የሚያስገኘውም ጊዚያዊ ፍሬ ሳይሆን ዘላለማዊ ነው፡፡ እናም ወደዚህ የአትክልት ሥፍራ መጥቼ ይህንን ፍሬ እለቅምና ፈውስ ወደ ሚያስፈልጋቸው ወደ ብዙ ሥፍራዎች እልከዋለሁ፡፡ አያችሁ በዚህ ፍሬ ውስጥ ብዙ ፀጋዎች ተከማችተዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ውጤት የመጣው በፍቅርና በመታዘዝ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህም ፀጋው ለሌሎች ጥቅም የሚውል የሚበላ ፍሬ ይዞ ይመጣል፡፡

"አ! ለሁላችሁም ላጫውታችሁ የምወደው ሚስጥራቶች አሉ! እጅግ ብዙ ሚስጥራትና አስደናቂነታቸው የማያልቅ ነገሮች አሉ፡፡ የመንግስተ ሰማያት ሥራዎችና መንፈሳዊ ህይወት ማለቂያ የሌለው ነው፡፡ አያችሁ መታዘዝ የመንግስተ ሰማያትን ዓይነት ሁኔታ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡ በእርግጥም መንግስቴ መጥቷል፣ ፈቃዴም እየተፈፀመ ነው፡፡ እናም አጋንንቶች

እነዚህን መንፈሳዊ የአትክልት ሥፍራዎች ይጠሏቸዋል፡፡ ለዚህም እንዴት አድርገው እንደሚያጠፏቸው ያለማቋረጥ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

"ይህንንም ለማድረግ በአብዛኛው የሚጠቀሙት የራስን ፈቃድ በራስ ወዳድነት መልኩ መፈፀምን ነው፡፡ ደስታን የሚሰጥ ምግብ ራስ ወዳድነትን ያመጣል፡፡ ደግሞም በአለም ውጤታማ መሆን ይህንን ሊያነሳሳው ይችላል፡፡ ለራስ ደስታን የሚያመጣ የትኛውም ነገር የአትክልቱን ሥፍራ የሚያጠፉ ትላትሎችና ጎጂ ነፍሳቶችን ይፈጥራል፡፡ የደስታ ትላልሎች የአበባውን ግንድ ያጠፋል፡፡ በራስ ጉዳይ የመጠመድ ትንንሽ ነፍሳቶች ደግሞ አበባዎቹን በመቀንጠብ ቀስ በቀስ ውበታቸው እንዲጠፋና እንዲወይብ ያደርጋሉ፡፡ የትምክህት ሻጋታ ደግሞ በስሮቹ ላይ በማደግ አበቦች እንዳያፈሩና ያሉም ፍሬዎች መቆየት እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል፡፡

"ሌሎቹን አጥፊ ነፍሳትን ሁሉ በአትክልቱ ሥፍራ በፊት ለፊት ማየት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን በሥሩ ላይ የሚበቅለውን ሻጋታ በእትክልቱ ቦታ ማየት አትችሉም፡፡ ትምክህት ባለበት ፍሬዎችና አበባዎች ብዙም አይቆዩም፡፡ አንዴ ትምክህት በአትክልቱ ሥፍራ ከገባ ሁሉም ይጠፋል፡፡ አትክልቱን ለማጥፋት ጠላት የመጀመሪያ እርምጃ የሚወሰደው በዚህ በኩል ነው፡፡ ትምክህት ሁሉን ነገር እንዳልነበረ ያደርጋል፡፡ በዚህም ምክንያት በመንገዳችሁ ላይ ዘላለማዊ ፍሬ ማፍራት አትችሉም፡፡

"አሁን ወደ ታዛዥነት እንመለስ፡፡ ያለፈው ሳምንት ብዙ ሙሽሮቼ ታዛዦች ነበሩ፡፡ በእርግጥም በእምነትና በመታዘዝ ለእኔ ብለው ሁሉን ነገር እንደማይጠቅም በማድረግ አለምን ትተዋል፡፡ አንዳንዶቹም ፍሬያቸው በስሏል፡፡ በቤተሰብ ውስጥ ፈውስ ሆኗል፣ ከእኔ ጋር የጠለቀ ግንኙነት፣ የአይምሮ ሰላምና የልብ ደስታ አግኝተዋል፡፡ ራስ ወዳድነት የሌለበት ፍቅር በዙሪያቸው አብቧል፡፡ በራሳችሁ ህይወት ይህንን ፍሬ አላያችሁም? ምናልባት ከአለም ጋር ግንኙነታችሁ ተቋርጦ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በእኔ ምን ያህል የበለጠ አገኛችሁ?

"እንዲህ በማድረጋችሁ ከተጠቀማችሁ ሁልጊዜ አሉታዊና አለማዊ ነገርን ብቻ ከሚያወራ ከዚህ ከመገናኛ ብዙኃን ራሳችሁን ቀስ በቀስ ነፃ ማውጣት አለባችሁ፡፡ ይህ በአለም ደረጃ ጠላት ሆን ብሎና አስቦ የሚፈፅመው ነገር ነው፡፡ በዚህም አስፈሪ ሁኔታን በመፍጠር ብዙ ሰዎች ያለማቋረጥ እንዲፈሩና ደህንነት እንዳይሰማቸው በማድረግ ጥፋትን እንዲያስከትሉ ለማድረግ ነው፡፡

"የኔ ሙሽሮች ለእኔ መቀደስ ከፈለጋችሁ በቅድስና መኖር አለባችሁ፡፡ አለምን ወደዚያ ጥላችሁ የቅድስናን ህይወት ማቀፍ አለባችሁ፡፡ በዚህ ውሳኔያችሁ የሚገኘውን ፍሬ መንግስተ ሰማይ ካልሆነ በቀር ምን እንደሆነ ማሰብ እንኳን አትችሉም፡፡ ስለዚህም አሁን አበረታታችኋለሁ፡፡

"ለሙሽሮቼ የተወሰነ ዓላማ ያላቸው እንዲሆኑ ይህንን ፀጋ አካፍላቸዋለሁ፡፡ ይህም ሁሉንም የአለም አረም በመግረዝ የቅድስና እርምጃ መራመድ እንዲችሉና የዘላለም ፍሬን እንዲያፈሩ የሚያስችል ነው፡፡

## መልዕክት ሠላሳ ሰባት
## መንግስተ ሰማያት ፡ ኢየሱስ ስለ አምልኮ ስለ ምግብና መዝናኛ የገለፀው

{Heaven: J Jesus shares about worship, food and recreation}

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ኦ! የኔ የዋህ ከምድር ተለያይተሽ የምትመጪበትን ጊዜ እንዴት በጉጉት እየጠበኩ መሰለሽ! ይህም እስከ መጨረሻው የምትመጪበትን ማለቴ ነው፡፡"

"ይህንንም ስል እስከመጨረሻው ማለቴ ነው፡፡ በዚህም የአንቺን ሙሉ መሰጠት አገኛለሁ፡፡ ደግሞም እጥብቀዋለሁ፡፡"

*ወደ ላላ መሬት ለመሄድ እየተገፋሁ በነበርኩ ወቅት የተሰጠኝን ሙሉ ትኩረት መቼም ይሰጠኛል ብዬ ገምቼም አላውቅም፡፡*

እሱም እንዲህ በማለት መለሰ . . . "ከአሁን ወዲያ ወደዚያ መወሰድም የለብሽም እዛው በላላ መሬት ላይ ትሆኛለሽ፡፡"

*እኔም እንዲህ አልኩ . . . ትኩረት እንዲኖረኝ ለማድረግ ጣፋጭ መጠጤን መጠጣት የለብኝም አይደል?*

"አይ ፣ ቢሆንም ግን በዚያም ሆነ በዚያ መጠጦቹ ይኖሩሻል፡፡ ይህም ከሰማይ ተራሮች ከተገኙ ፍሬዎች የሚሰሩ ናቸው፡፡ ደግሞም አይስክሬሞቹ ከዚህ አለም ውጪ ናቸው፡፡"

*እኔም 'እጠራጠራለሁ' አልኩት*

" እኔ እየተናገርኩ ያለሁት እውነቱን ነው፡፡ በምድር ላይ በፍፁም ቀምሰሽ የማታውቂው ዓይነት አይስክሬም ነው፡፡ ለዚህ ቃል እገባልሻለሁ፡፡ እንደዚያ ዓይነት አይተሽም አታውቂም፡፡"

*የመካከለኛው ምስራቅ ሰዎች ምግብ ቤት አንዴ የቀመስኩት የአበባ ጣዕም ያለው አይስክሬም በጣም ወድጄዋለሁ፡፡*

"ኦ የዛን ዓይነት ይኖርሻል፡፡"

*ይህ በሰማይ እንዴት ነው የሚሰራው? ማለቴ ወጣ ያለ ነገር ነው፡፡ . . . ጨዳራና አብሮት ያለ ነገር ሁሉ?*

"በእርግጥ ማወቅ ትፈልጊያለሽ?"

*አንተ ልትነግረኝ እስከፈለከግህ ድረስ፡፡*

"በትክክል እነግርሻለሁ፡፡ በሰማይ ሰውነትሽ አጅግ ቀላልና እውነተኛ ነው፡፡ ከሰው የሚወጣ ቆሻሻ የሚባል ነገር በዛ የለም፡፡ የውኃ ማጠራቀሚያና ሽንት ቤት የሚባል ነገር የለም፡፡

*ዋው! ያ ግልግል ነው*

"ጥሩ ብለሻል፡፡ ግልግል ቋሚ ሁኔታን የሚያመለክት ነው፡፡ እራስሽን ከምንም መገላገል አያስፈልግሽም፡፡"

*ቢቃላት መጫወት ትፈልጋለህ አይደለም?*

"እኔን ነኝ የፈጠርኳቸው ልበልሽ?"

*ትችላለህ፡፡ እውነቴን ነው፡፡*

"ምክንያቱም የምትኖሩት በሌላ ወርድ /Dimension/ ስለሆነ ከጎለመሱ በኋላ/beyond maturity/ ማደግም ሆነ መበስበስ የለም፡፡ የሚሞቱ ሴሎች፣ ባክቴሪያዎችና እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች የሉም፡፡ በአግባቡ ለመናገር ምግብ በደስታ ይበላል፣ ነገር ግን 'በሰውነታችሁ' ውስጥ እንዳሸተታችሁት ዓይነት አልፎ ይሄዳል፡፡ በሰውነታችሁ ላይ የሚኖረው ውጤት በጣም ጥቂት ነው፡፡ መልካሙ ዜና ከጣፋጭ ምግቦች የተነሳ መወፈር የለም፡፡ ሁልጊዜ ቀጭንና እኔ እንድትሆኑ እንደፈጠርኳችሁ ፍፁም ነው የምትሆኑት፡፡ የሆርሞን መዛባት የለም፡፡ ከአካባቢ የተነሳ በሰውነት ላይ ይህም በአይምሮም ላይ ሆነ በስሜቶች ላይ የሚመጣ ተፅዕኖ የለም፡፡ ንፁህ፣ ስምምነት ያለው ደስታና ተድላ ነው፡፡"

*አ! ኢየሱስ ይህ በሚሆን ጊዜ ሁሉ 7ኛው ሰማይ ላይ እደርሳለሁ፡፡ እናም የምወደው ኪቦርዴና ሴሎው ይናፍቁኛል፡፡*

"የኔ ፍቅር ርዕሱን መቀየር ትፈልጊያለሽ?"

*"አ! አንተ እኮ ፍፁም የምትሰብ ጨዋ ሰው ነህ!"*

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . በሰማይ ሁሉ ነገር የሚከናወነው በማሰብና በመፈለግ ነው፡፡ ሁሉም ፍላጎቶች ንፁህና እግዚአብሔራዊ ናቸው፡፡ ምግብን በደስታ ለመብላት መፈለግ እንኳን እግዚአብሔራዊ ነው፡፡ እንዳውም በዚህ መንገድ ባስቀምጠው ይሻላል፡፡ ምግብን ለመብላት ደስ መሰኘት እጅግ እግዚያብሔራዊ ነው፡፡ ለምን? ምክንያቱም የእኔ ደስ መሰኘት የሚመነጨው እናንተ ደስ መሰኘታችሁን በማየት ነው፡፡ ምክንያቱም ልቤ ሁሉ ነገራቸውን በሰጡኝ ፍቀር ተሞልቷል፡፡ ስለሆነም ሁሉ ነገሬን ለመስጠት ፍላጎቴ ነው፡፡ በዚህም ደግሞ ምስጋና ሲያቀርቡልኝ እኔን ከፍ ማድረግና ማምለክ ነው፡፡

"ይህንን እንድገልፅላችሁ ፍቀዱልኝ፡፡ አያችሁ ምንጩ እኔ መሆኑኔን በማወቅ ስታደንቁ፣ በእውነት ከልብ ስታደንቁ፣ ማንኛውንም ነገር ስታደንቁ በእውነቱ ከሆነ እያመለካችሁኝ ነው፡፡ በምድር በምትኖሩበ ወቅት ብዝ ነገሮችን እንድትተዉ እነግራችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም *ሥጋዊና* ምድራዊ ተፈጥሮአችሁ እንዲሁም አካባቢው ሁሉ በኢጋንንት የተሞላ ነው፡፡ ስለዚህም በቀላሉ ከቁጥጥር ውጪ በመሆን ፍላጎታችሁን በምድራዊ ነገር ሊበላሽ ይችላልና ነው፡፡ በሰማይ ግን እንዲህ ዓይነት ነገር የለም!! እዛ አንበሶቻችሁን ስትዳስሱ፣ ጣፋጭ መጠጦቻችሁን ስትጠጡ፣ በሚዘምሩላችሁ ዛፎች ስትደሰቱ ማየት እኔንም ያስደስተኛል፡፡

*ዛፎች ለእኛ ይዘምራሉ?*

ኦ! አዎ፣ ለእናንተ መዘመር ደስ ይላቸዋል፡፡ ፍጥረታት ሁሉ እንደሚዘምሩ አታውቂም? በሰማይ የሚሰማውን የሙዚቃ እርግብግቦሽ መጠን/ frequency/ ለመስማት ገና ስለማትችይ ነው፡፡ በሰማይ ግን ሁሉንም ዓይነት መርገብገቦች/ frequencies/ መስማት ትችያለሽ፡፡ ኦ፣ ክብር! በሰማይ የሚጠብቃችሁ ነገር ሊገባችሁ ከሚችለው በላይ ነው፡፡ ነገር ግን ጥቂቱን ቆንጥሬ ሳካፍላችሁ ደስ እያለኝ ነው፡፡

*ጌታ ወደ ምግቡ ብንመለስ?*

"በርዕሱ ላይ ምን የሚወራ ተጨማሪ ነገር ይኖራል? ምግብ ለማዘጋጀት የተቀጠሩ ሰዎች አሉ፡፡ ምክንያቱም ምግቡን በጣዕምና በንፅህና የሚያዘጋጁት በፍቅር ስሜት ሲሆን ነው ምግቡን ለመብላት ፍላጎት የሚያድርባቸው፡፡ ነገር ግን በሰማይ ምግብ በጭራሽ ትኩረት ሊሆን አይችልም፡፡ ሁልጊዜ! የሁሉም ትኩረት በአብ ክብር ላይ ነው፡፡ ከጂሲ ዱፐሌት እንደሰማችሁት እኛ ሁልጊዜ በቋሚነት ከአንዳችን ወደ አንዳችን እንመላለሳለን፣ እንሄዳለን፣ እንመጣለን፡፡ በዚህም የፍቅር ልውውጡ ከትንሽ ፍጥረት ጀምሮ ተመልሶ በሰማይ ውስጥ ያስተጋባል፡፡ ቀጭኑ ሳር እንኳን የአምልኮን ድምፅ ያሰማል፡፡

"ምግብ መመገብ አምልኮአዊ ቢሆንም እንኳን ነፍሶች ወዲያው የሚሳቡት ወደ አብ በመሆኑ የእርሱን መገኘት ይናፍቃሉ፡፡ ይህም በመሆኑ ምግብ የመብላቱ ደስታ እርሱን በማምለክ ወዲው ይተካል፡፡ አያችሁ፣ ነገሩ በክብ መልክ የሚፈፀም ነው፡፡ ሁሉ ነገር ተመልሱ ወደ አብ ይመለሳል፡፡ እናም ወደ እኛ ይመለሳል፡፡ አካባቢው ወይም ሁኔታው እንዲሆን የተፈጠረው የእናንተ ፍላጎት ወዲያው አድናቆቱን ወደ ምንጩ እንዲያደርግ ነው፡፡ እናም ምስጋናውን ለእኛ ታቀርባላችሁ፡፡ ስለዚህም አካባቢው በቋሚነት በአምልኮ የተሞላ ነው፡፡ ነገር ግን ንፁህ የሆነ አምልኮ በመሆኑ ከምንም ጋር ሊወዳደር አይችልም፡፡ ስለዚህም ሁሉም ዙፋኑ ባለበት ክፍል ለመሆን ይፈልጋል፡፡

*ነገር ግን ይህ እንዴት ይሆናል? ማለቴ እንዴት ሁሉም በዙፋኑ ክፍል ውስጥ ተጠቃሎ ሊገባ ይችላል?*

"በደስታ ሳቀና፣ ይህ አንቺ መረዳት ከምትችይው በላይ ነው፡፡ ወርዶች / dimensions/ አሉ፣ ከየወርዶች ውስጥ ሁልጊዜም አንድ ተጨማሪ ቦታ ይኖራል፡፡ ነገር ግን ይህንን አስታውሺ፣ በሰማይ እያንዳንዱ የሚያገለግለው በተለያዩ ችሎታዎች መጠን ነው፡፡ ምንም እንኳን አንድ ነፍስ እስኪፅናና ድረስ መጠበቅ ባይኖርበትም የእያንዳንዱ ግለሰብ አምልኮና ጊዜ እጅግ ስርዓት ያለው ነው፡፡ መፅናናት ሲፈለግ ሁልጊዜ ይፅናናል፡፡

*ነገር ግን በሰማይ ማንም የሚሰቃይ ያለ አይመስለኝም ነበር?*

"እዛ ያለው ሁልጊዜ ደስታ ነው፡፡ ነገር ግን ግንዛቤ ልትጨብጡ የሚያስፈልገው ነገሮች ገና አላለቁም፡፡ ገና የሚሰራ ሥራ አለ፡፡ እናም ገና ባላለቁ ጉዳዮች ላይ የሌላውን ስሜት መጋራት ይኖራል፡፡ የሌላውን ስሜት መጋራት ደግሞ ህመም አለው፡፡ ህመም ካለ ደግሞ መፅናናት ያስፈልገዋል፡፡ ለማለቅ ገና በሆኑ ነገሮች ላይ አንዱ የሌላውን ኃዘን ይጋራል፡፡

*ጌታዬ ይህ ብዙ ጊዜ የሚከሰት ነገር ነው?*

"እንደ አጋጣሚ ሆኖ እስከ ሚሊኒየሙ መጨረሻ ድረስ ከምንፈልገው በላይ ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉም በሥራ ላይ እንዲሰማራ የሚያደርገው አንዱ ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን ህመሙ እንደ ምድር ዓይነት የጨለመ፣ የሚያስፈራና የሚጨቁን አይደለም፡፡ በፍፁም እንደዛ አይደለም፡፡ በሰማይ ተስፋና መፍትሔ አለ፡፡

"የሚያስፈልጉ ነገሮች ብዙ አሉ፡፡ ሁሉም በቋሚነት ምድር ላሉ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ፀሎት ይደረጋል፡፡ ፈውስ ይካሄዳል፡፡ ሙዚቃ ከሰማይ ቀጥታ ወደ ምድር ይለቀቃል፡፡ በሰማይ ላሉ ዜጎች ምንም የሚያስፈልጋቸው ነገር የለም፡፡ የሚያስፈልገው ሁሉ ተትረፍርፎ ይገኛል፡፡ ነገር ግን በምድር ለሚኖሩትና ወደዚህ ለሚሻገሩት መላዕክቶችና ቅዱሳን የሚያዩት የሚያስፈልጋቸው ነገር አለ፡፡ አሁን በዚያን ጊዜ ስለሚሆነው ነገር ብዙ ወደ ውስጥ ገብቼ ለማውራት አልፈልግም፡፡ ይህንን ማለት ብቻ በቂ ነው፡፡ ሁሉም እኔ በመስቀሉ ላይ የሰራሁትን የማዳን ሥራ እንዲፈፀም ነፍሶችን ለማዳን በትልቅ ንቃትና ትኩረት የሚንቀሳቀሱበት ይሆናል፡፡

"አንዳንድ ጊዜያት አሉ የሰማይ በሮች የሚዘጉበት ፡፡ ይህ ለተወሰነ ጊዜ ሥራን በማቆም ራስን ማከም ወይም የማገገሚያ ጊዜ /retreat time/ ልንለው እንችላለን፡፡ በዚህ ጊዜ በምድር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ባለማወቅ ዕረፍት የሚወስድበት ጊዜ ነው፡፡ ይህንንም የሚወስነው እግዚአብሔር አብ ነው፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ ከሰማይ ውጪ የሚሆነውን ነገር ባለማወቅ የሚቆይበትና ብዙ ደስታና ግብዣ የሚካሄድበት ነው፡፡

*"ጌታዬ እኔ እኮ በሰማይ ማንም መቼም የሚደክመው ያለ አይመስለኝም ነበር፡፡*

ኦ! አይደለም፡፡ ያ በትክክል ያለመረዳት ነው፡፡ በሰማይ ሁልጊዜ መፅናናትና መታደስ አለ፡፡ ነፍሶችን ለማዳን በሚደረገው ሥራ ከባድ ጉዳት ሊኖር ይችላል፡፡ በተለይም ይህ የሚሆነው መንፈሳዊ ውጊያ እየተካሄደ ባለበት ጊዜ ነው፡፡ በእናንተ አባባል ሁሉም እንደ 'ኤሌክትሪክ' ሆነ የምትሉት ማለት ነው፡፡ በአንደኛው ሰማይ ላይ  የእሳት ብልጭታ እንዴት የጦርነት ምልክት እንደሆነ እኔ እንዳሳየሁሽ(የእኛ ከባቢ አየር ነው) ሲሆን ማለት ነው፡፡ በዚን ጊዜ ጉዳት የሚያስከትሉ የኃይል /energies/ ልውውጦች ይካሄዳሉ፡፡ ነገር ግን በሰማይ ሁልጊዜ ጥገና ይካሄዳል፡፡ ደግሞም በሰማይ ጋደም ብሎ ለመዝናናትና ራስን ለማደስ አልጋዎች አሉ፡፡ ብዙዎች በምድር ያልለመዷቸው የኃይል እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡ ለምን መሰለሽ በጫካ ውስጥ በዛፍ ላይ የሚጠለጠለውን ተወዛዋዥ መተኛ /**hammock** / ያዘጋጀሁት?

*ጌታ ያንን በፍፁም አስቤውም አላውቅም፡፡*

"ኦ!  አዎ፣ ራስን ለማደስና ለመዝናናት ብዙ እንደነዚህ ዓይነት ጊዚያቶች ይኖራሉ፡፡ ክሌር ለእያንዳንዱ ነፍስ ልዩ በሆነ መልኩ ያዘጋጀሁትን ነገር በምድር ሆኖ ማሰብና መረዳት አይቻልም፡፡ በእውነት ለመናገር ከፍቅሬ የተነሳ ያዘጋጀሁላቸውን አይተው በመደነቅ ሲመለከቱት ማየት እፈልጋለሁ፡፡

"የኔ ሙሽራ አሁን ወደፊት ሊመጣ ያለውን ደስታ በትንሹ እንድታዩ አድርጌሻለሁ፡፡ ይህም ጨለማው ሊገለጥ ሲያንዣብብ በፍርሃት እንዳትዋጡ ነው፡፡ በእንፃሩ ተስፋ የገባሁላችሁን በማሰብ ደስ ይበላችሁ፡፡ ጨለማው እያየለ በመጣ ቁጥር መምጫዬ መድረሱን እወቁ፡፡  ዛሬ ማታ የማካፍላችሁ በፈተና ውስጥ ባለፋችሁ ጊዜ እንኳን የማያልቀውን ደስታ የሚያመጣውን ችሎታ ነው፡፡ ለምወዳችሁ ለእያንዳናዳችሁ እጄ ስለሰራቻችሁ ለነፍሳችሁ የሚያስፈልገውን ለማካፈል እፈጥናለሁ፡፡ አይን ያላየው ነገር ግን አሁን የነገርኳችሁን በልባችሁ ውስጥ ቆልፋችሁ ያዙት፡፡ ደግሞም ሁልጊዜ አሰላስሉት፡፡

## መልዕክት ሠላሳ ስምንት
## ፍቅር በመንግስተ ሰማያት የዋጋ መተመኛ ቅንጣት ነው

{In heaven, love is the valued particle}

"የኔ አገልጋዮች እንዲሆኑ ትልቅ ዋጋ ከምሰጠው አንዱ ሐቀኛ መሆናቸው ነው፡፡ ከእውነት ጋር አብሮ የሚኳዝ፣ እጅግ የረቀቀ ነገር ግን ኃይል ያለው መርገብገብ /vibration/ አለው፡፡ 'እውነት የራሱን ፀጋ ይዞ ይጓዛል' እንደተባለ፣ እውነትን በምትናገሩ ጊዜ ያ መርገብገብ /vibration/ ወደ እዛ ነፍስ ልብ ዘልቆ ይገባል፡፡ እዛም በመቀመጥ የዛ ሰው አንድ ክፍል ይሆናል፡፡

"ለአገልጋዮቼ ሁሉ የምመኘው ማስመሰላቸውን ትተው ሐቀኞች እንዲሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ገና ከልጅነት የተማራችሁት ድካማችሁን እንድትደብቁና ጠንካራ፣ ፍፁምና ስህተት አልባ ሆናችሁ እንድትታዩ ነው፡፡ የዚህም ውጤት በቀላሉ ሊጠቃ የሚችለውን፣ ስስና፣ ለስላሳ የሆነውን የውስጠኛውን ማንነት ለመጠበቅ ባዕድ ግድግዳንና አስመሳይነትን መገንባት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ህብረተሰቡ ለመኖር የፈጠረው ዘዴ /survival mechanism/ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ በምድር ባለው በእኔ መንግስት ቦታ የለውም፡፡ እናንተ ስህተት የምትሰሩ ሰዎች እንጂ እግዚአብሔር አይደላችሁም፡፡ ስለዚህ እነዚህን ስህተቶቻችሁን በደበቃችሁ ጊዜ ሁሉ ራሳችሁንና የሌሎችን መንፈሳዊ እድገት ታቀጭጫላችሁ፡፡

"ስህተቶች በፊት ለፊት በግልፅ ሲወጡ ያንን ለማስተካከል ሥራ ይሰራል፡፡ ምክንያቱም ስህተቶቹ ጉዳትን የሚያስከትሉና ሌሎቹም ሰዎች ጉዳቱ እንዲቀጥል መፍቀድ የማይችሉት ስለሆነ ነው፡፡ እኔም እነዚህን ችግሮች የማስተካክላቸው በገሃድ ነው፡፡ ስለዚህ እናንተንም የምጠይቃችሁ በተመሳሳይ መንገድ እንድታደርጉት ነው፡፡ በሰዎች መካከል መተባበር ወይም አንድነት ከሌለ ሊደረስባችሁ የማይቻል ደሴቶች፣ ድብቆች፣ በጨለማ የተከበባችሁ፣ በኃፍረት የተሞላችሁ፣ በቀላሉ የማትገኙና ዝግ ነው የምትሆኑት፡፡ በዚህ ዘመን ያለው ህብረተሰብ እንዲህ ዓይነት ሆኗል፡፡ ነገር ግን በሰማይ እንዲህ አይደለም፡፡ በሰማይ ሐሳቦች ሁሉ ግልፅና ለሁሉም የሚታዩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ርህራሔ የተትረፈረፈ በመሆኑ ቸርነትን ለማድረግና መፅናናት ለሚያስፈልገው መፅናናትን ለማድረግ ሁሉም ስለሚሯሯጥ ነው፡፡

*ጌታ ሆይ እኔ ግን እኮ በሰማይ ምንም ስህተት የማይኖርብን ይመስለኝ ነበር!*

"ኦ እንደሱ አይደለም፡፡ በሰማይ በብዙ መልኩ በጥልቅና በመረዳት ገና ማደግ የሚያስፈልጋችሁ ነገር አለ፡፡ እዛ የሌለው ኃጢያትን መስራት ነው፡፡

*ጌታ ይህንን ለመረዳት በጣም ከባድ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔ ሁልጊዜ ስሰማ የነበረው በሰማይ እኛ ፍፁም፣ ሙሉ፣ነገራችን ሁሉ የተስተካከለና ምንም ጉድለት የማይኖረን እንደሆነ ነው፡፡ ይህንን ከተናገርኩ በኋላ ግን ህዝቦችን የሚፈውሰውን የህይወት ወንዝ ትዝ አለኝ፡፡ ይህ ከሆነ ጉድለት እንደሚኖረን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ስለዚህም ፈውስ መካሄድ አለበት፡፡*

"የኔ ፍቅር በሰማይ የሚያስፈልገው እውቀት ሁሉ ይቀርብላችኋል፡፡ እውቀትንም ስትጠይቁ ይሰጣችኋል፡፡ ጥበብ ግን የሚያድግ ችሎታ /acquired quality/ ነው፡፡ ስለዚህም ጥበብን ለማካበት ጊዜና ልምምድ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ምድር ግን ትልቅ የጥበብ እጥረት አለ፡፡ በአንፃሩ ግን እያንዳንዱ ነፍስ የማያልቅ መረዳትና ፍቅር ሊኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህንን ማግኘት የሚቻለው በመጠየቅ ሲሆን የሚለቀቀውም ቀስ በቀስ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አንድ ነፍስ ስለ አንድ ነገር ረሃብ ሲኖረው ስለዚያ ነገር መጠየቅ ይጀምራል፡፡ በሰማይ ይህ ሁልጊዜ የሚከናወነው ከፍቅርና ከፈውስ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው፡፡ በሰማይ ሁሉ ነገር የሚደረገው ከውስጥ በመነጨ ፍቅር ምክንያት ነው፡፡

*ከመሳሪያ ፣ ከህንፃ፣ ከኃይልና ከመሳሰሉት ጥበቦች ጋር በተያያዘስ?*

"አዎ እነዚህም ነገሮች ቢሆኑ መነሻቸው የውስጥ ፍላጎት መሆን አለበት፡፡ የዚህም ፍላጎቱ መነሻው ህይወትን ለማሻሻል፣ ለመርዳትና ለማጎልበት መሆን አለበት፡፡ የእነዚህ ስጦታዎች መነሻ ግንዳቸው ፍቅር ነው፡፡

*ጌታ ልክ ይህንን ሲናገር ትንቢት ቢሆን ፣ እውቀት ቢሆን፣ ጥበብ ቢሆን ሁሉም ይሻራል፣ ፍቅር ግን መቼም አይሻርም የሚለውን ቃል ትዝ አለኝ፡፡*

"ፍቅር የዋጋ መተመኛ ቅንጣት /Valued particle/ ነው፡፡ ሌላው ሁሉ ነገር ከፍቅር ቀጥሎ የሚመጣና ለፍቅር የሚገዛ ነው፡፡ የሰማይ የውስጥ ፍላጎትና ፅናትም ፍቅር ነው፡፡ በሰማይ መነሻው ፍቅር ያልሆነ ምንም ነገር አይገኝም፡፡ ሳይንቲስቶችም ለመለየትና ለመያዝ የሚፈልጉት ይህንን ቅንጣት/particle/ ነው፡፡ ለእነርሱ እንዲህ እላለሁ . . .'ፍቅር የእግዚአብሔር ስለሆነ ሊያዝ አይችልም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊጨበት ስለማይችል ነው፡፡ ጊዚያችሁን የምታባክኑት እንዲሁ ነው፡፡' እኔ በዚህ ዓይነት መንገድ የቀረፅኩት ከመጀመሪያውኑ የሰው ነፃ ፈቃድ እንዴት እንደተበላሸ ስላወቅሁና በመጨረሻውም እስከዚህ ጥግ እንደሚደርስ ስለማውቅ ነው፡፡

" አሁን ሐቀኝነት፣ ግልፅኝነትና ለጥቃት መጋለጥ ወደሚለው ሐሳብ እንመለስ፡፡ በዚህ ቻናል እንዲታይ የምፈልገው ግልፅነት፣ እውነተኛ መሆን፣ አደጋና ቅድመ ሁኔታ የሌለው በተግባር የሚገለፅ ፍቅር መሆኑን ነው፡፡ ሰዎች መሳሳታቸውን በግልፅ ሲናገሩ እናንተም ስህተታችሁን አንዳችሁ ለአንዳችሁ በግልፅ ተነጋገሩ፡፡ በዚህም አንዱ ሌላውን መረዳትና ፈውስ፤ ከመለያየት ይልቅ የመተባበር ወይም የአንድነት ስሜት ይኖራል፡፡

አያችሁ ይህ መለያየት ነው ሰዎችን ወደማይፈለግ ቆሻሻ የሚወስደው፡፡ ስህተታቸው በግልፅ ወጥቶ መፍትሔ ካላገኘ በአለም ለመኖር ምክንያት ያጣሉ፡፡ ስለዚህም ሁለት ዓይነት ህይወት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ተቀባይነትን ለማግኘት ለሌሎች የሚያሳዩት ህይወትና በእውነት በውስጣቸው የሚካሄደው እውነተኛው ማንነታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ማንነቶች እርስ በርስ ሲታረቁ ሙሉና የተፈወሳችሁ ትሆናላችሁ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁለቱ እንደተለያዩ የምትኖሩ ከሆነ ለመታመምና ለእድገት ማነቆ የሚሆን ችግር እንዳለ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አታድጉም፣ ወደፊት መሄድ አትችሉም፡፡ ምክንያቱም እናንተ በቋሚነት ያንን ጨለማችሁን እየጎተታችሁና እየሸፋፈናችሁ ነው፡፡

በቋሚነትም እንዲህ እያደረጋችሁ ማደግም ሆነ ወደፊት መጓዝ አትችሉም፡፡ ይህም በውስጣችሁ በእውነት እናንተ የሆናችሁትና በውጪ ደግሞ ምንም እንዳልጎደለው ሆኖ ለመታየት መሞከራችሁ ነው፡፡ ይህ ሁለት ዓይነት ሰው ሆኖ መኖር የማያልቅና እጅግ አድካሚ ነው፡፡ ስለዚህም በጣም ቀላሉ ነገር ራሳችሁን መሆንና ግልፅ መሆን ነው፡፡

"በዚህ ቻናል ላይ ያለኝ ዓላማ ነፍሶች ከስህተት ጋር መታገል ምንም እንዳልሆነና ኩነኔ ሳይሰማቸው ስህተታቸውን ለማረም እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ነው አንዱ ለሌላው መጋቢና ጉልበት ሰጪ በመሆን እውነተኛ ፍቅር የሚገለጠው፡፡ የተረገጠውንና ደካም የሆነውን በደግነት የሚያፅናናን ነፍስ ለማየት እንዴት እወዳለሁ! በሰማይ ያለ ይህንን ቸርነት በምድር በተግባር ሆኖ ለማየት እንዴት እወዳለሁ! ሰማይን የጎበኙ በሙሉ በዛ ሐሳብ እንዴት በግልፅ ለሁሉም እንደሚታይ ያውቃሉ፡፡ በተግባርም እንዳያችሁት ችግር በሚፈጠር ጊዜ ሁሉም ለማፅናናት እንዴት እንደሚረባረቡ አይታችኋል፡፡"

*አዎ እኔም እንደዚህ ዓይነት ገጠመኝ አለኝ፡፡ እንደተረዳሁት ከሆነ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ቅዱስ ቤተሰቦች ሲሆኑ እነርሱጋ ራት ተጋብዤ ሄጄ ነበር፡፡ እነዚህም ሰዎች ህይወታቸውን ሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጡ ነበሩ፡፡ ሁላችንም በጠረጴዛው ዙሪያ ተሰብስበን እያለን አንዲት ለየት ያለች፣ ፅሑፏን በጣም የማደንቅላት ሴት መጥታ በኢየሱስ ፊት ለፊት ተቀመጠች፡፡ እኔ ደግሞ የተቀመትኩት በኢየሱስ በግራው በኩል ነበር፡፡ እኔም በዚች ሴት ቀናሁ፡፡ በዛ ክፍል ውስጥ የነበረ ሰው ሁሉ መብላቱን አቆመ፡፡ ይህቺ የቀናሁባት ሴት ቆመችና እኔን ለማቀፍ ወደ እኔ ሮጣ መጣች፡፡ ሁሉም ሰው በምድር እያሉ ይቀኑ እንደነበርና በሰማይ ግን እንደዚህ ዓይነት ስሜቶች እንደማይኖሩ በመናገር አፅናኑኝ፡፡*

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . " በትክክል ያንን ነው እኔም አሁን እያወራሁ ያለሁት፡፡ ቅናት እጅግ አስቀያሚ ስሜት ሲሆን የብዙ ኃጢያቶች ሥር ነው፡፡ ማንም ሰው መቅናት አይፈልግም፡፡ ነገር ግን ለዚህ አስቀያሚ ስሜት አንቺን ከመኮነን ይልቅ ሁሉም አንቺን ለማፅናናትና ወደ አንቺ ሮጡ፡፡ እነሱም በእንደዚህ ዓይነት ህይወት ተፈትነው እንደነበረ ተናገሩ፡፡

"እያችሁ በምድርም አንዱ ለሌላው ስህተቱን እንደዚህ ቢናገርና የፈውስ ፀሎት ቢቀበል ኖሮ በሽታ በጠፋ ነበር፡፡ እኔ በምድር ህይወት እንዲሆን የቀረፅኩት በዚህ መልክ እንዲሆን ነበር፡፡ ነገር ግን በራስ ላይ ካለ ከፍተኛ አመለካከት የተነሳ፣ ከክብር የተነሳ፣ ከስግብግብነት የተነሳ ሰዎች ስህተትን በመሸፈን የኃጢያት ህይወት ይመራሉ፡፡

# መልዕክት ሰላሣ ዘጠኝ
# መንግስተ ሰማያት የማያልቅ ደስታ የሚገኝበት ሥፍራ ነው

{Heaven is a place of perpetual joy}

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ስለ ሽልማታችሁ የበለጠ እንድታስቡ እፈልጋለሁ፡፡ ጊዜው እየጨለመ ሲሄድ፣ አሁን እንኳን እየጨመረ ነው፣ አይምሮአችሁን በሰማያዊ ነገሮችና እኔ በገባሁላችሁ ቃል ላይ ማተኩር መልካም ነው፡፡ መንግስተ ሰማያት ኃይል በፍፁም አያልቅም፡፡ ተስፋ መቁረጥ ሳይኖር ተነሳሽነት ያለበት፣ በቀላል ግባችሁን መፈፀም የምትችሉበት፣ ሁልጊዜ በደስታ የተሞላ ፊት በዙሪያችሁ የምታገኙበት፣ ህይወትን በደስታ መኖር እነደ መተንፈስ ቀላል የሆነበት፣ ለእኔ ምስጋናና ክብር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ አንድ ደቂቃ እንኳን ሳይቀርብ የማይቀርበትና ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ አምልኮ ያለበት ነው፡፡"

*ኢየሱስ ሰዎች በገነት ጊዜ እንደሌሉ ይናገራሉ፡፡*

እሱም ሳቀና "ያንን ሐሳብ ከየት ነው ያገኙት? እኔ አልፋና ያሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፣ የነበረውና ያለው፣ ደግሞም የሚመጣው፣ ሁሉን ቻይ ነኝ ፡፡ በዚህ ጥቅስ ብቻ እንኳን ጊዜ ሁለት ጊዜ ተገልጿል፡፡ እንዴት ነው በመካከል ምንም ነገር ሳይኖር መጀመሪያና መጨረሻ የሚኖረው? እንዴትስ ነው ኃላፊ፣ አሁንና ወደፊት የሚኖረው? ነገር ግን ልኬቶች/dimensions/ ይሽከረከራሉ ። "

ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብኩ. . . 'ኦ! ይህ በጣም ከባድ ይሆንብኛል ሊገባኝ የሚችል ነገር አይደለም።'

እሱም እርማት ሰጠኝና እንዲህ አለ . . . "ዝም ብለሽ አዳምጪ፡፡ ምናልባት ከባድ ላይሆን ይችላል፡፡ እንዲገባሽ ለራስሽ ዕድል ስጪ።"

*እሺ*

"አጠቃላዩን ፅንሰ ሐሳብ በሐሳብ ደረጃ ስላልገለጥኩልሽ ብቻ ያ ነገር እውነታ አይደለም፣ አንቺም በአይምሮሽ ልትረጂው አትችይም ማለት አይደለም፡፡ አንቺ በሚገባሽ መነገድ ስለማስረዳሽ ልብ ብለሽ አድምጪኝ፡፡

"ልኬቶች/ dimensions/ ይሽከረከራሉ ማለቴ የተለያዩ ጊዚያቶች ይመጣሉ ደግሞም ከዕይታ ይጠፋሉ ማለቴ ነው፡፡ በመንግስተ ሰማያት ለመቁጠር አንድ ብላችሁ እንኳን ለመጀመር የሚያዳግታችሁ እጅግ ብዙ ልኬቶች አሉ፡፡ እኔ የፈጠርኩት እያንዳንዱ የህይወት ክፍል የራሱ ለኬት አለው፡፡ ይህም የተፈጠረበት የራሱ የመኖር ልዩ ሁኔታ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ እያንዳንዱ ልኬት ደግሞ እርስ በርሱ የተቆላለፈ ነው፡፡ ይህም የተቆላለፈበት ንድፍ/pattern/ ሁሉም በአንድነት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል፡፡ የዚህን ምሳሌ ለማየት ልዩ ልዩ ቀለማትና ቅርፅ ያላቸው ቁርጥራጭ ጨርቆች በአንድ ላይ ተገጣጥመው የአልጋ ልብስ ሆነው እንደተሰፉ ዓይነት የፍጥረታትን ልዩ ልዩ ልኬቶች በዚህ መልኩ ማየት እንችላለን፡፡ በዛ ውስጥ ግን እያንዳንዱ በግልና በህብረት ውስጥ ያለውን ህልውና ምን እንደሆነ መናገር ይችላል፡፡ ፎቶ ለማንሳት ካሜራችሁን ስታስተካክሉ ብዙ የተለያዩ ነገሮች በዕይታው ውስጥ አሉ፡፡ ነገር ግን በእኔ ምርጫ ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባችሁ ትደረጋላችሁ፡፡ የህይወት እንቅስቃሴ ሁልጊዜም አለ፡፡ ነገር ግን ዕይታችሁ የሚወሰነው እኔ ለእናንተ ትኩረት እንድታደርጉ ባደረግሁት ነገር ላይ ነው፡፡"

*ወደፊት አሁንም አለ፣ ነገር ግን ከእኔ ዕይታ ውጪ ነው እያልከኝ ነው ያለኸው ?*

"በትክክል"

*ግን እኮ ይህ ማለት የንጥቀትን ትክክለኛ ቀን ታውቀዋለህ ማለት ነው፡፡*

"አ! ይህንን እንደምትይ በምን አውቃለሁ"

*በግምት?*

"በጣም ያስቃል፡፡ አባቴ ባስቀመጠው ገደብ በመስማማቴ ቀኑን አላየውም፡፡ አሁን ገባሽ?"

እም ....

ኢየሱስ ከዚህ በተጨማሪ የምትለው ነገር አለህ? ለመናገር የምትፈልገው ምንም ነገር ቢኖር ለመስማት እወዳለሁ፡፡

" *መንግስተ ሰማያት የማያቋርጥ ደስታ ያለበት ነው ስል፣* እያወራሁ ያለሁት በመንግስተ ሰማያት ለዘላለም ተያይዞ፣ እርስ በርሱ ተቆላልፎ ልዩ ልኬት ያለውን ነው፡፡ ዘላለም አያልቅም፡፡ አይደለም?

*አዎ፡፡ በእኔ ትርጉም ኢያልቅም፡፡*

"ስለዚህም ይህ የምነግርሽ በአንቺ መረዳት ትክክል ነው፡፡ ምክንያቱም በመንግሰተ ሰማያት የዓይን ትኩረት በዘላለም ላይ ነው፡፡ በምድር የዓይን ትኩረት በአላቂው ጊዜ ላይ ነው፡፡ በመንግስተ ሰማያት በጣም ደስተኛ የምትሆኚው ሙላቱ /fullness/ ነው፡፡ በቋሚነት ሰፊ ነው፡፡ ዓይንሽ ማየት እስከሚችለው ድረስ ደስታ ነው፡፡ ለዘላለም የአበቡ አበባዎች የሚገኙበት ነው፡፡ በዚህ ምድር ግን አበቦች ያብባሉ ደግሞም ይረግፋሉ፡፡ በኃጢያት ምክንያት የተወሰነባቸው የህይወት ዙሪት/ life cycle/ አለ፡፡ በዚያም ህይወትንና ሞትን ተራ በተራ ያስተናግዳሉ፡፡ ኃጢያት ሲነሳ ግን ህይወት ዘላለማዊ ይሆናል፡፡

*"ነገር ግን ኢጋንንቶች የሚኖሩት ለዘላለም ነው፡፡ እናም ለዘላለም አስከፊና ኃጢያተኞች ናቸው፡፡ ይህ እንዴት ነው የሚሰራው?*

"እኔ የፈጠርኩት ማንነት የማይሞት ነው፡፡ በዚህ ምድር ያሉ አበቦች ሰውነታቸው በህይወት ዙሪት ይለዋወጣል ምክንያቱም በምድር ላይ ለከንቱነት ስለተዳረጉ ነው፡፡ በመንግስተ ሰማያት ግን እንዲህ አይደለም፡፡

*እያልክ ያለኸው በመንግስተ ሰማያት የፈጠርከው የትኛውም አበባ ለዘላለም ነው የሚኖረው፡፡*

"በትክክል"

አ! በጣም ብዙ አበቦች ናቸው!

*መንግስተ ሰማያት እጅግ ሰፊ ሥፍራና ያልተነገሩ ውስጣዊ ወርዶችና ስፋቶች ወይም ልኬቶች ያሉት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ* በእኔ ፍቅርና ደስታ የተያያዙ ናቸው፡፡

# መልዕክት አርባ
# የሚሊንየሙ አስተዳደር

{Governement in the millennium}

"ብዙዎቻችሁ እየቀረበ ያለውን ታላቁን የመከራ ዘመን በትልቅ ፍርሃትና መቀጥቀጥ እየተመለከታችሁት ነው፡፡ አዎን በእርግጥም ዘመኑ ሊወዳደረው የሚችል የሌለ የሐዘን ወቀት በመሆኑ በዚህ መልኩ ልትመለከቱት ይገባል፡፡

"በዚያን ወራት እግዚአብሔር ከፈጠረው ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያልሆነ ደግሞም የማይሆን የመከራ ዓይነት ይሆናልና።" ማርቆስ 13፡19

"ነገር ግን ይህ የሚሆነው የኔ መንግስት በዚህ ምድር ላይ እንዲገለጥ መንገድ መጥረግ ስላለበት ነው፡፡ ክፉ መታሰርና ተይዞ መቀመጥ አለበት፡፡ በዚህም እኔ እንድትሆኑ እንደፈጠርኳችሁ ጥቁር ነጥብ የሌለው ፍጡር ሆናችሁ ታድጋላችሁ፡፡ ምድርን ለእናንተ ውብ፣ ምቹና ደስታን የምትሰጥ አድርጌ የፈጠርኳትን ነገር ግን ስግብግብነት ያበላሸውን፣ ምድርን ከሚያጠፉ ኬሚካል፣ ክፉ ሰዎች ካመጡት በሽታዎች፣ እንዲሁም መሬትን ባዶና የማትመች ካደረገት ከኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች መንፃት አለባት፡፡ ልጆቼ መንገዱ መጠረግ አለበት፡፡ ይህ በሚሆን ጊዜ ግን የሚያስደስት አይደለም፡፡

"የኔ መንግስት የሚያደርገው ነገር ሁሉም ወደፊት መጥተው እንዲያድጉ፣ እንዲስፋፉ፣ እንዲፈጥሩና በዚህም ለሰው ልጆች የሰጠኋቸውን ስጦታዎች በሙላት በመግለጥ በደስታ ተግባርያዊ እንዲያደርጉት ማድረግ ነው፡፡ ግብርናው፣ ኢንዱስትሪውና ትምህርቱ እኔ መልሼ የገነባሁትን ምድር በውበቱ እንዲቀጥል የሚያደርግ ሆኖ ማየት እንዴት ደስ የሚል ነገር ነው?

"የእጅ ባለሞያዎች፣ ፖለቲከኞች፣ ገበሬዎችና አስተማሪዎች ሁሉም ሊያከናውኑት የሚገባ ሥራ ይሰጣቸዋል፡፡ አሁን የምትሰሩት ሥራ ሁሉ ያን ጊዜ ያለ ብልሽት የምታከናውኑት ይሆናል፡፡ ከሁሉም ነገር ትልቁ ትኩረታችህ ለእኔ አምልኮ በመስጠት ላይ ይሆናል፡፡ ትኩረታችሁ የሚሆነው እውቀት፣ ኃብት፣ ውበት ወይም ያላችሁ ችሎታ ላይ ሳይሆን ወንድሞቻችሁንና እኔን በመውደድ ላይ ይሆናል፡፡ ኦ! ይህ ሁሉንም ነገር እንዴት ይቀይራል? የመረረን ነገር ጣፋጭና የሚያጎለብት ይሆናል፡፡ የሚጨቁናችሁ ወይም የማይረዳችሁ የለም፡፡ በአንፃሩ ግን ሁሉም የሚያስፈልጋችሁንና ፍላጎታችሁን ለማድረግ ዝቅ ይላል፡፡ ይህም ልክ እናንተ የአገልጋይ ልብ እንዳላችሁና ዝቅ እንደምትሉት ማለት ነው፡፡ በዚህም ሰዎችን በማገልለገል ትልቅ እርካታ ይገኛል፡፡ መጥፎ ድርጊት የሚፈፅሙ ደግሞ በአንፃሩ ይነቀፋሉ፡፡ ይህም ቢሆን ግን እያንዳንዱ ሰው በራሱ ልዩና አስደናቂ መንገድ ያንፀባርቃል፡፡ ይህም የሚሆነው የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ሳይሆን በእነርሱ ውስጥ ያለውን የኔን ህይወት በማብራት ክብር ለመስጠትና ፍሬዎቹን ለማሳየት ነው፡፡

"የራሳቸውን ጥቅም የሚፈልጉ፣ የሚሰርቁ፣ የሚዋሹና ሌሎችን ሰዎች የሚያጭበረብሩ ተገምግመው በልግስናና በታማኝነት እንዲሄዱ ይማራሉ፡፡ ማንም ሰው ቢሆን ማንንም መጨቆንና ሌላውን መጉዳት አይፈቀድለትም፡፡

"ፍትህና ምህረት አስባችሁት በማታውቁት ዓይነት በዚህ ወቅት ይገኛል፡፡

"በንጥቀት የሚወሰዱት አስተዳደራዊ ሥራውን በመላዕክቶቼ ረዳትነት ይሰራሉ፡፡

በፊተኛው ትንሣኤ እድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ። ራዕይ 20፡6

"በአዲሱ ምድር እያንዳንዱ ነፍስ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በዛ ማንም የማይፈለግ ወይም ሥራ የሌለው ሆኖ አይገኝም፡፡ ሁሉም ሊሰራው በተሰጠው ሥራ ደስተኛ ይሆናል፡፡ አ! ወደፊት ብዙ የምናየው ነገር ይኖራል፡፡

"ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት ግን ክፉ እንዲጠፋና በምድር ላይ ሚዛናዊነት እንዲመለስ የኔ ፍትህና ቁጣ መለቀቅ አለበት፡፡ ሰዎች ስግብግብነት የሚያስከትለውን ማየት አለባቸው፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ኃጢያት ሞት እንደሆነ መማር አለባቸው፡፡ እናም ኃጢያት የሚያደርጉ ሟቾች እንደሆኑ ማወቅ አለባቸው፡፡

የኃጢያት ዋጋ ሞት ነውና፣ የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም ህይወት ነው፡፡ሮሜ 6፡23

"በዚህ ወቅት ማንኛውም ኃጢያት የሚመነጨው ከሰው ፈቃድ ብቻ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ሰይጣንና ተከታዮቹ ሁሉ ከዚህ ከከብረ ህብረተሰብ ተለይተው ይታሰራሉ፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን አንዳንዶች በግትርነት ሌሎችን በመጉዳት የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚፈልጉ፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶች በመንግስቱ ውስጥ ገብተው ለመሳተፍ ብቁ እስኪሆኑ ድረስ ስለ ህይወት ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ወደ ትምህርት ቤት ይገባሉ፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ ምህረቴ ይቀድማል፡፡

"ይህንን እየነገርኳችሁ ያለሁት ፊት ለፊታችሁ ያሉ ጊዚያቶች ጨለማና አስቸጋሪ ስለሚመስሉ ነው፡፡ አዎ በእርግጥም ጨለማና አስቸጋሪ ናቸው፡፡ ከማዕበሉ በኋላ ግን የምህረቴ ቀስተ ደመናና መልካምነቴ በምድር በሚኖሩ የሰው ልጆች ሁሉ ላይ የሚፈፀምበት ይሆናል፡፡ ይህንን ጊዜ ለማየት እንዴት እናፍቃለሁ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ከምህረቴ በፊት ስለሚሆነው እንዴት አዝናለሁ፡፡

"ልጆቼ ግን ይህንን ልታውቁ ይገባል፡፡ በማዕበሉ ወቅት እንኳን ምህረቴ በሥራ ላይ ነው፡፡ ለሚወዱኝና ትዕዛዜን ለሚጠብቁ አዛኝ፣ አፍቃሪና መሃሪ ነኝ፡፡ ከእናንተ ውስጥ የዋሆችና እንደ ህፃናት የሆኑት ሊቀርቡኝ ይችላሉ፡፡ እንደ ህፃናት የዋህ፣ ቀላልና ንፁህ ለመሆን ለመረጡት አባት እሆናቸዋለሁ፡፡ ብልህ ጎልማሳ ለመሆን ለመረጡት ደግሞ እኔ የብልህነታቸው ፈጣሪና አምላክ ነኝ፡፡ ለተስፈንጣሪዎችና በኃይላቸው ለሚንቀሳቀሱ ደግሞ እኔ የኃይላቸው ሁሉ አምላክ፣ በክብር የተሸፈንኩና ማንም ሊደርስብኝ የማይችል ነኝ፡፡

"ለፍጥረቴ ጉልበቴን ዝቅ አድርጌያለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግሁት ሁሉም በእኔ ዘንድ እንደታወቁ ያህል እንኳን እንዲያውቁኝ ነው፡፡ ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ። 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡12

"ስለዚህም በሁሉም ነገር እኔን በመምሰል በአካባቢያችሁ ለሚገኙ ሁሉ ምንም ወደኋላ ሳትሉ ሙሉ ምህረትን አድርጉ፡፡ በምህረትን የሚመላለሱ ነፍሶች በፍርድ ጊዜ ትልቅ ምህረት ይቀበላሉ፡፡ ስለዚህም ለእናንተ መልካም እንዲሆንላችሁ ሌሎች ለእናንተ እንዲደረግላችሁ የምትወዱትን አድርጉላቸው፡፡

በዚህ መልእክት ጊዜ ሁሉ ወደ አይምሮዬ የመጣው ቃል፡-ነገር ግን ክብር በምድራችን ያድር ዘንድ ማዳኑ ለሚፈሩት ቅርብ ነው፡፡ ምሕረትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ። እውነት ከምድር በቀለች፥ ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች። እግዚአብሔርም በጎ ነገርን ይሰጣል፥ ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች። ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፥ ፍለጋውንም በመንገድ ውስጥ ያኖራል።(መዝሙር 85፡9-13)

# መልዕክት አርባ አንድ
# ህይወት ኢየሱስ በሚገዛበት በሚሊኒየሙ መንግስት

{Life during Jesus' rule during the millennium}

" እኔ በምድር ላይ ለመግዛት ስመጣ(ታላቁ የመከራ ዘመን ካለቀና የሚሊኒየሙ ጊዜ ሲጀምር) እኩልነትና ፍትህ በአለም ሁሉ ላይ ይሆናል፡፡ ከአሁን ወዲያ መንግስታት የትኛውንም የሰው ዘር፣ የትኛውንም ከለርና የትኛውንም እምነት የሚከተሉትን እንዲገቷቸው፣ ዝቅ እንዲያደርጓቸው አልፈቅድም፡፡ ምንም እንኳን ምድር በእኔ እውቀት ብትሞላና ክብሯ ቢሆንም የሰው ራስን የመውደድ አባዜ እንደገና በማቆጥቆጥ በስግብግብነት የሌሎችን ነፃነት ለመግፈፍ ይነሳሉ፡፡

"ይህንን እኔ አልፈቅድም፡፡ ስግብግብነት የነበረውን ሁሉ እንዳልነበር የሚያደርግና ሁሉን ነገር ከመልካም ወደ ክፉ የሚቀይር ነው፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን(ጌታ እያወራ ያለው እስከ ሚሊኒየሙ ማብቂያ ያለውን ነው) ብዙ ውበትና ሰላም ታገኛላችሁ፡፡ ትውልዱ በመልካም ፈቃድ ሁኔታ ያብባል፡፡ ለሰው ልጆች ያቀድኩት እውነተኛው እምነት ሁሉን ወደ እኔ የክብር ብርሃን በማምጣት ለእኔ መኖር እንደ ዓየር መተንፈስ ቀላል ይሆናል፡፡ ደስታ በቤተሰብ፣ በመንደርና በከተሞች መካከል እንኳን ይሰፍናል፡፡ ይህም የሰው ልጆች እኔንና ፍቅሬን ለማወቅ ስለቻሉና በግልፅም በመመስከራቸው ነው፡፡

"የአሜሪካ ምዕራቡ ክፍል ከሁሉም የአገሪቷ ክፍሎች ሳይወድም የሚቀረው ክፍል ነው፡፡ ከዚህም ክፍል አዲስ መንግስት ይነሳል፡፡ ይህም አንዱ ምክንያት ነው የሎው እስቶን የአገሪቷን ምዕራቡንና የምዕራቡን ደቡብ ክፍል ሙሉ ለሙሉ እንዲያጠፋ የማልፈቅደው፡፡ በእግዚአብሔር መመሪያ መሰረት፣ በመልዕክቶቼ እንዲሁም ለማስተዳደር አደራ በሚሰጣቸው ሰዎች ፈፃሚነት በእነዚህ የአገሪቷ ክፍሎች እርሻና ቴክኖሎጂ ከፍታቸውን ይይዛሉ፡፡ ለማስተዳደር አደራ የሚሰጣቸው ሰዎች ሁሉንም ለማስተዳደር ተገቢና ብቁ መሆናቸውን፣ ከራስ ወዳድነትና ከተደበቀ የውስጥ ፍላጎት የፀዱ መሆናቸውን ያስመሰከሩ ሰዎች ናቸው፡፡

“ይህ አሁን ካለው ጋር ይለያያል፡፡ አሁን ያለው ሙብቀል የጀመረው ከጥንቆላ የውስጥ ፍላጎት በሮም ገና ከመጀመሪያው የጀመረ ነው፡፡ ሮም እያልኩ ስናገር የማወራው ስለመንግስቱ እንጂ ስለ ቤተ ክርስቲያን አይደለም፡፡

"ቤተ ክርስቲያኔን መልሶ ለመገንባት የሚነሳው ከአካሌ ውስጥ በሰፍርንና በከተሞች ለመምራት ከተመረጡት ውስጥ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ስብስቦች ትንንሽ ሆነው እንዲቀጥሉ የሚደረጉት፡፡ ከአንዳንድ ልዩ ስብሰባዎች በቀር፡፡ እነዚህም ስብሰባዎች እኔ ራሴ በመገኘት አዲስ መረዳቶችን ለማከፈል፣ መገለጦችን፣ አንዱ ከሌላው ጋር እንዴት በሰላምና በፍቅር እንደሚኖር፣ የማካፍልበት ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ገና ከጅማሬው እኔ ከመሰረትኩት ውጪ ሌላ አማራጭ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፡፡ ይህ ጉልበቱ የማይበረከክ ያለመርካት ዘር ነው፡፡ ይህንን አማራጭ የሚፈልጉ አባቶች ናቸው አመፁን የሚያነሳሱት(በሚሊኒሙ መጨረሻ)፡፡ ክሌር ከሰው ልጆች ውስጥ ክፉን እስካወጣ ድረስ ስግብግብነትና ትምክህት ሁልጊዜም ይኖራል፡፡

" እኔ ስላዘጋጀሁት ስለ ወደፊቱ ተስፋ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ የኔ መንግስት በዚህ ምድር ላይ እስኪመሰረት ድረስ ረኸሮም፣ ጨለማና ደም መፋሰስ የበዛበት መንገድ አለ፡፡ ሁላችሁም እንድታውቁት የምፈልገው ይህ ይመጣል፣አይቀርም፡፡

ነገር ግን ለትውልዱ ገና የሚመጣ ትልቅ ተስፋ አለ፡፡ ሰላም በወንድማማቾች ፍቅር ይመሰረታል፡፡ የእያንዳንዱ አገር ማንነትና ባህል እንደተጠበቀ ቢሆንም በተፈጥሮ ኃብትና በኃይል አቅርቦት ምክንያት የሚደረግ ጥልና ጭቅጭቅ አይኖርም፡፡ በቀላሉ አነጋገር ይህ ዓይነቱ ድርጊት ተቀባይነት የለውም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት አይፈቀድም፡፡ የሰው ተፈጥሮ ምን ጊዜም በዛ አቅጣጫ መሄድ ይቀናዋል፡፡ ነገር ግን እኔ እውነተኛ ነፃነትና ፍትህ ለሁሉም ተግባርያዊ እንዲእንዲተገበር አደርጋለሁ፡፡ በጣም ትንሹ እንኳን ቢሆን አንድም ሰው ዝቅ ተደፈርጎ እንዲታይ አልፈቅድም፡፡ ለዚህም መንፈሴ ሁሉ ነገር በትክክል ተከናውኖ እንደሆነ፣ ለድሆች፣ ለታናናሾችና ለተገለሉ ፍትህ በትክክለኛው መንገድ ተፈፅሞ እንደሆነ በምድር ሁሉ ላይ ይመለከታል፡፡

"የኔ ሙሽራ በዚያን ጊዜ በዚህ ሥራ ላይ ተካፋይ ትሆኛለሽ፡፡ ለአንቺ እጅግ የሚያስደስት ሥራ አለኝ፡፡ ደስታሽ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ይሆናል፡፡

*"እኔ እኮ የመሰለኝ አገራት ሁሉ የሚከፋፈሉ ነው፡፡*

"አዎ አገራት በእርግጥ ይከፋፈላሉ፡፡ ነገር ግን አንዱ ከሌላው ያለው ርቀት እጅግ ትንሽ ነው የሚሆነው፡፡ ምናልባት ጀልባ ያስፈልግሽ ይሆናል ከአንዱ ወደ ሌላኛው ለመሻገር፡፡ እያንዳንዱ አገር የራሱ የሆነ የአየር ፀባይ፣ ባህል፣ ልምድና ፋብሪካ ይኖረዋል፡፡ የንግድ ልውውጥ በአገሮች መካከል ይኖራል፡፡ ከአሁን ወዲያ በምንም ዓይነት መንገድ የሰው ልጆች በነዳጅ አይጣሉም፡፡ ምክንያቱም ልክ ምድር እንደነፃች አዲስ የኃይል መዋቅር ይዘረጋል፡፡

*ዋው! ይህንን በጣም ለማየት የምፈልገው ነገር ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ክፍያ የለ! የጋዝ ክፍያ የለ!*

"የመገናኛ ዘዴ ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ ቀላል ይሆናል፡፡ ብክለት ያለፈ ታሪክ ሆኖ ይቀራል፡፡ ማንም ቢሆን በፍጥረታቴና በሰዎች ልጆች ላይ ጥፋትን ሊያመጣ የሚችል ሥራ እንዲሰራ አይፈቀድለትም፡፡ ይህም ቢሆን ግን ሰዎች ይህንን ያማረ ህይወታቸውን በሞኝነት ሊጫወቱበት ይፈልጋሉ፡፡ እኔም የፈለጉትን እንዲያደርጉ፣ አንድ ላይ ተከማችተውና ታስረው ከምድረ ገፅ እንዲጠፉ እፈቅዳለሁ፡፡

*ጌታ እዚህጋ የሚናገረው በሚሊኒየም መጨረሻ የሚካሄደውን የአርማጌዶን ጦርነት ነው፡፡*

*ጌታ በእውነት ከሆነ እኔ በደንብ እንዲገባኝ የምፈልገው የወደቁ መላዕክቶች ተልዕኮ ምን እንደሆነና አንተ ደግሞ ምን ለማድረግ እንዳሰብክ ነው፡፡*

"እነሱ ያላቸውና ያዳበሩት ቴክኖሎጂ የተጣመመ፣ ክፉና እጅግ አስቀያሚ ነው፡፡ ሁሉም ለዚህ የተነሳሱት ከስግብግብነት፣ ከጥላቻና ለስልጣን ከላቸው ከፍተኛ ጉጉት፣ እንዲሁም ለመልካም ነገር ፍፁም ግዴለሾች በመሆናቸው ነው፡፡ እኔ እነዚህን አንዱም ሳይቀር ሁሉንም ጠራርጌ አጠፋቸኋለሁ፡፡ ከእኔ ጋር ለመወዳደር በመጣር ፍጥረታትን መፍጠራቸውን ለማወጅ ከተነሱ ከእነዚህ አታላይ ኢጋንንቶችና ከተጣመሙ ቴክኖሎጂዎች ከአሁን ወዲያ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ አይኖርም፡፡ የእነሱ ችሎታ ፍጥረታትን ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ በቃ ይኸው ነው፡፡

የእናንተ መንግስት ገዝቶ ያስገባው ነገር በህይወታቸው ላይ፣በነፍሳቸው ላይና በዘራቸው ላይ ሊስተካከል የማይችል ኪሳራ ያስከትልባቸዋል፡፡ ሁለተኛም ለስልጣን ማሰራራት አይችሉም፡፡ አለም ሁሉ ወደታች ተገልብጦ እንደሚጠነፈፍ ክፉ ሁሉ ከምድሪቷ ላይ ይራገፋል፡፡ ይህንን እኔ ስመጣ የማየው ይሆናል፡፡ ልክ እኔ ከመምጣቴ በፊት የሶስት ቀን ጨለማ ይሆናል፡፡

በእነዚህ ቀናት ሰው ሁሉ ምንም ተስፋ የለም በቃ አለቀልን ብሎ ተስፋ የሚቆርጥበት ጊዜ ነው፡፡ በእነዚህ ቀናት ውስጥ መላዕክቶቼን በመላክ እያንዳንዱን የክፉ ወኪል፣ የማስፈራሪያና የማጥፊያ አጀንዳቸውን እንዲያጠፉና እንዲያስሩ አደርጋለሁ፡፡

ከዚህ ወቅት በኋላ ህይወት አዲስ ይሆናል፡፡ ኤደን ገነት በምድር ሁሉ ላይ ታድሳ እንደገና እንደመጣች ያህል ነው የሚመስለው፡፡ እነዛ ቀናት ያመጡት ብርሃን የኔን ምህረትና ክብር ያውጃሉ፡፡ በዚህ ወቀት በብዙ የምድሪቷ ክፍሎች ቅፅበታዊ የሆነ እንደገና መብቀል ይሆናል፡፡ በእርግጥም ክፋት ከእንግዲህ በኋላ መግዛት የማይችልበት አዲስ የንጋት ቀን ነው፡፡ ሰዎች ሁከትንና ክፋትን ይፈልጓቸዋል፡፡ ነገር ግን ሁሉም እንዲያርፉ ስከተደረጉ አያገኟቸውም፡፡

*ዝሙትን የሚፈፅሙ፣ ውሸታሞች፣ ሌቦች ...ወዘተ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ አይገቡም የተባለውስ?*

"እንደዚህ የተበላሸ ህይወት ያላቸውን መልሶ ለማቋቋም ብዙ ጥረት ይደረጋል፡፡ ለሚፈልጉት የኔ ፍቅር፣ ደግነትና ምህረት ስለሚያነፃቸው ይፈወሳሉ፡፡አዲስ ህይወት እንዲጀምሩ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ በቂ አቅርቦት ይደረግላቸዋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቹ አሮጌው አካሄዳቸውን መቀጠል ይፈልጋሉ፡፡ በዚህም ቅጣታቸውን ያገኛሉ፡፡ በእኔ መንግስት ውስጥ ክፉ ሰዎች ክፋትን እንዲያባዙ አልፈቅድም፡፡ ትክክለኛውንና መልካሙን ነገር የሚከተሉትን ሰዎች ከማበላሸታቸው በፊት እንዲያቆሙ ይደረጋሉ፡፡

ይህ እየነገረን ያለው ቅጣት ከሚሊኒየሙ በፊት በምድር በሚኖሩት የሚከናወነውን የምድርን ነፍሶች የማንፃት ወቅትንና እንዲሁም በሚሊኒየሙ ማለቂያ ሊሆን ያለው እንዲሆን የሚፈቅደውን ወቅት አያጠቃልልም፡፡

"መጓጓዣዎች ለኃብታሞች ብቻ የሚሆንበት ጊዜ ያበቃል፡፡ ሁሉም ሰው የተሰጠውን ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስችለውን ነገር በበቂ ለማግኘት እኩል መብት አለው፡፡ ቀድመው ውጤታማ የሆኑና በህጌ የሚኖሩ ደግሞ ሌሎችን ለማንሳትና ለመርዳት ሥልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም የተወለዱበትን የመጀመሪያ ዓላማቸውን እንዲያሳኩ ይደረጋሉ፡፡

"ምንም ከልካይ ነገር የለም፡፡ ፖለቲካ፣ አድልዎና ጉቦ የለም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ነገር በእኔ መንግስት ውስጥ ተቀባይነት የለውም፡፡ሁሉም የራሱ ድርሻና ደስተኛ ሆኖ ለመኖር የሚያስችለው በቂ ነገር ይኖረዋል፡፡ አያችሁ ኮሚኒዝምም የነበረው ሐሳብ ይህ ነበር፡፡ ነገር ግን በሰው የተበላሸ ተፈጥሮ ምክንያት ለመውደቅ ግድ ነበር፡፡ ከእኔ ህግና ስርዓት ውጪ እንደዚህ ዓይነት ነገር ሊፋፋ፣ ሊያድግና ቀጣይ ሊሆን አይችልም፡፡ ሰው ሁልጊዜ የሚያመዝነው ራስን ወደ መውደድ ነው፡፡ በዚህም ውጤታማ እየሆኑ ያሉ ሰዎች እነርሱ የገነቡትን ለመስረቅ በሚፈልጉ ጠንካራ ሰዎች ወደታች ይረገጣሉ፡፡

*ስለ አዲስ ሰማይና ስለ አዲስ ምድርስ ምንድነው ያለው?*

"አዲስ አደርጋቸዋለሁ፡፡ የነበረ እንዳልነበር፣ የነበረ መሆኑ እንኳን እስከማይታሰብ ድረስ ይሆናል፡፡

"በልቤ ውስጥ እንዳለው እንደዛው ወዲያው አደርጋለሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ ሰው ሁሉ ጌታን ክብር ያያል፡፡ የነበር ከአሁን ወዲያ የለም፡፡ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ፡፡"

*የባህር ፍጥረታትስ?*

